https://chilot.me



## አዋጅ ቁጥር /2012

## የግል ዳታ ጥበቃን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የግል ህይወት መከበር እና መጠበቅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የተረጋገጠ መብት፤ እንደዚሁም ግለሰቦች በግል ዳታ ላይ ያላቸው መብት በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የዚህ መብት አንድ አካል በመሆኑ፤

የግል ዳታ ጥበቃ መርሆችን በማስቀመጥና የግል ዳታ የሚቀናበርበትን አግባብ በመወሰን የግል ዳታ ጥበቃ ባህልና አሠራርን ለማዳበር አስቻይ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣቱና የዚህን የሕግ ማዕቀፍ የማስፈጸሚያ ሥርዓት መፍጠሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነጻነቶችን ለመጠበቅ፣ እንደዚሁም ውጤታማ የሆነ የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ መሠረታዊ በመሆኑ፤

የዳታ ባለቤቶችን መብቶችን፣ የዳታ ተቆጣጣሪና አቀናባሪዎች ግዴታዎችን፣ እንደዚሁም በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በመደንገግ ጠንካራ የግል ዳታ ጥበቃ ሥርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ ቁ......./2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ

(1) “ተደራሽ የሆነ ሪከርድ” ማለት የጤና፣ የትምህርት፣ ወይም ሌላ ለሕዝብ ተደራሽ የሆነ ሪከርድ ነው፤

(2) “ውክልና የተሰጠው ተቋም” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባራት ለመፈጸም ኮሚሽኑ ውክልና የሰጠው መንግሥታዊ ተቋም ነው፤

(3) “ባዮሜትሪክ ዳታ” ማለት የአንድን የተፈጥሮ ሰው የአካላዊ፣ የፊዚዮሎጂ እና የባህርይ መለያዎችን መነሻ በማድረግ፤ ይህን ሰው በተለየ መንገድ ለመለየት ወይም ይህ ሰው እሱ መሆኑን በተለየ መንገድ ለማረጋገጥ የሚረዳ ከታወቀ የቴክኒክ ማቀናበር ሂደት የተገኘ የገጽታ ምስል፣ የጣት አሻራ፣ የዓይን ብሌን አሻራ፣ ወይም ሌላ እነዚህን የሚመስል የግል ዳታ ነው፤

(4) “ሕጻን” ማለት ዕድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ የዳታ ባለቤት ነው፤

(5) “ኮሚሽን” ማለት የኢትዮጵያ የግል ዳታ ጥበቃ ኮሚሽን ነው፤

(6) “ፈቃድ” ማለት የዳታ ባለቤት የግል ዳታው እንዲቀናበር ያለውን ፍላጎት በነጻነት፣ መረጃ ላይ በመመሥረት እና ጥርጣሬ በማያስነሳ መልክ፤ በጽሑፍ ወይም በሌላ በማንኛውም አዎንታዊ አግባብ፤ የተጠው ስምምነት ነው፤

(7) “ዳታ” ማለት፡-

(ሀ) በአውቶማቲክ መሳሪያ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ምላሽ በመስጠት በመቀናበር ሂደት ላይ ያለ፣

(ለ) ሪከርድ የተደረገው በፊደል (ሀ) በተጠቀሰው መሳሪያ እንዲቀናበር የታሰበ፣

(ሐ) የመዝገብ ሥርዓት አካል ሆኖ ወይም የመዝገብ ሥርዓት አካል እንዲሆን ታስቦ ሪከርድ የተደረገ፣ ወይም

(መ) በፊደል (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ሥር የማይወድቅ ነገር ግን ተደራሽ የሆነ ሪከርድ አካል የሆነ ኢንፎርሜሽን ነው፤

(8) “የዳታ ተቆጣጣሪ” ማለት ማንኛውም በራሱ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን የግል ዳታ የሚቀናበርበትን አግባብ የሚወስን ሰው ነው፤

(9) “የዳታ አቀናባሪ” ማለት የዳታ ተቆጣጣሪው ሠራተኛ ያልሆነና በዳታ ተቆጣጣሪው ቦታ ሆኖ ዳታ የሚያቀናብር ማንኛውም ሰው ነው፤

(10) “የዳታ ባለቤት” ማለት በግል ዳታ ላይ ባለቤት የሆነ ሰው ነው፤

(11) “የቀጥታ ማርኬቲንግ” ማለት በማስታወቂያ ወይም በሌሎች የሽያጭ ግብዓቶች አማካይነት በግለሰቦች ላይ ያነጣጣረ ኮሙኒኬሽን ነው፤

(12) “ዶኩመንት” ማለት

(ሀ) ዲስክ፣ የቴፕ ክር ወይም ሌሎች መገልገያዎች ማለት ሲሆን ከእነዚህ መገልገያዎች በሌሎች መሳሪያዎች ድጋፍ ወይም ያለድጋፍ ከስዕሎች ውጪ እንደገና ሊታይ የሚችል ኢንፎርሜሽን፤ እና

(ለ) ፊልም፣ የቴፕ ክር ወይም ሌሎች መገልገያዎች ማለት ሲሆን ከእነዚህ መገልገያዎች በሌሎች መሳሪያዎች ድጋፍ ወይም ያለድጋፍ እንደገና ሊታይ የሚችል ስዕላዊ ኢንፎርሜሽን፤

በውስጡ የያዘ መገልገያ ነው።

(13) “ምስጠራ” ማለት ከታሰበው ተቀባይ ውጭ የኤሌክትሮኒክ መልዕክትን ማንም ሰው ወይም ማሽን እንዳያነበው የማድረግ ሂደት ነው፤

(14) “የመዝገብ ሥርዓት” ማለት የተማከለ፣ ያልተማከለ ወይም አሠራርን ወይም መልክዓምድርን ወይም ሌሎች የታወቁ ቅድመ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ተደራሽ እንዲሆን የተዋቀረ የግል ዳታ ስብስብ ነው፤

(15) “የጄኔቲክ ዳታ” ማለት አንድ ግለሰብ የወረሳቸው ወይም ያገኛቸው አጠቃላይ ባህርያት ሲሆን፤ በተለይም ከግለሰቡ በተወሰዱ ባዮሎጂካዊ ናሙናዎች ትንተና መሠረት ስለዚሁ ግለሰብ ፊዚዮሎጂ ወይም ጤና፣ የተለየ ኢንፎርሜሽን የሚሰጥ የግል ዳታ ነው፤

(16) “ምክር ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤

(17) “ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል የተፈጥሮ ሰው” ማለት በተለይም ስምን፣ መለያ ቁጥርን፣ የቦታ ዳታን፣ የኦንላይን መለያን፤ ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑና ከዛ ሰው ጋር ተያያዥ ከሆኑ አካላዊ፣ የውስጥ ሰውነት፣ የጄኔቲክ፣ የአዕምሮ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል ወይም የማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር ተያያዥ የሆኑ መለያዎችን በመጠቀም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሊለይ የሚችል ሰው ነው፤

(18) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

(19) “የግል ዳታ” ማለት

(ሀ) ከዳታው፣ ወይም

(ለ) ግለሰቡን በተመለከተ የተሰጡ ማንኛውም አስተያየቶች እና ዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ሌላ ግለሰብ ይህን ግለሰብ አስመልክቶ ያላቸው ሃሳብ አመላካቾችን ጨምሮ፣ ከዳታው እና ሌላ በዳታ ተቆጣጣሪው ሥር ካሉ ወይም በእርሱ እጅ ሊገባ ከሚችል ኢንፎርሜሽን በመነሳት

ተለይቶ ከሚታወቅ ወይም ተለይቶ ሊታወቅ ከሚችል ሰው ጋር የተገናኘ ኢንፎርሜሽን ነው፤

(20) "የግል ዳታ ጥሰት" ማለት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመንቀሳቀስ ላይ ያለን፣ የተከማቸን ወይም በሌላ ማናቸውም አግባብ የሚቀናበር የግል ዳታን ድንገት ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ በመደምሰስ፣ በማጥፋት፣ ይዘቱን በመቀየር፣ ያለምንም ሥልጣን ለሌሎች ይፋ በማድረግ፣ ወይም ሌሎች እንዲያገኙት በማድረግ የሚፈጽም የደህንነት ጥሰት ነው፤

(21) "የአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጤንነት" ማለት ለአንድ ግለሰብ የተሰጡ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶችን የሚዘረዝርና ስለ ግለሰቡ የጤና ሁኔታ የሚገልጽ ኢንፎርሜሽን ነው፤

(22) "የፍርድ ሂደት" ማለት በፍርድ ቤት ውስጥ ወይም ጥላ ሥር የሚካሄድ ሂደት ሲሆን፣ በወንጀል ጥፋት ዙርያ የሚደረግ ምርመራን፣ እና የዲስፕሊን ሂደቶችን ይጨምራል፤

(23) "ማቀናበር" ማለት መሰብሰብ፣ ሪከርድ ማድረግ፣ ማደራጀት፣ ማዋቀር፣ ማከማቸት፣ ማስማማት ወይም መቀየር፣ ከተከማቸበት ማውጣት፣ ማማከር፣ መጠቀም፣ በማስተላለፍ በማሰራጨት ወይም በሌላ መንገድ ይፋ ማድረግ፣ አንድ ማድረግ ወይም ማዋሃድ፣ መገደብ፣ ማጥፋት ወይም መደምሰስን ጨምሮ በግል ዳታ ወይም በግል ዳታ ስብስቦች ላይ በአውቶሜትድ ወይም አውቶሜትድ ባልሆኑ መሳሪያዎች የሚደረግ ተግባር ወይም የተግባራት ስብስብ ነው፤

(24) "ፕሮፋይሊንግ" ማለት የግል ዳታን በመጠቀም የግለሰቦች ማንኛውም የግል ሕይወትን ለመገምገም በተለይም የዚያን ግለሰብ የሥራ አፈጻጸም፣ የኢኮኖሚክ ሁኔታ፣ የጤና፣ የግል ምርጫዎቹን፣ ፍላጎቶቹን፣ ታማኝነቱን፣ ባሕርይውን፣ መገኛ ቦታውንና ዕንቅስቃሴውን ለመተንተን ወይም ለመገመት በአውቶሜትድ መሳሪያ የሚደረግ የግል ዳታ ማቀናበር ነው፤

(25) "ሲዶኒማይዜሽን" ማለት ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን በመጠቀም ካልሆነ በስተቀር የግል ዳታ ከአንድ የዳታ ባለቤት ጋር እንዳይቆራኝ በማድረግ የግል ዳታን ማቀናበር፣ የግል ዳታው ተለይቶ ከሚታወቅ ወይም ተለይቶ ሊታወቅ ከሚችል ግለሰብ ጋር እንዳይቆራኝ ለማድረግ ተጨማሪ ኢንፎርሜሽኑ ለብቻው እንዲቀመጥ፣ እንደዚሁም የቴክኒክ እና የአደረጃጀት እርምጃዎች ሥር እንዲወድቅ ማድረግ ነው፤

(26) "ተቀባይ" ማለት ዳታው ይፋ የተደረገለት ወይም ተደራሽ የተደረገለት ማንኛውም ሰው ነው፤

(27) "ማቀናበርን መገደብ" ማለት የተከማቸ የግል ዳታ ወደፊት እንዳይቀናበር ለማድረግ መለየት ነው፤

(28) "ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ" ማለት የአንድ ሰው

(ሀ) ዘርን ወይም ብሔርን፣

(ለ) የጄኔቲክ ወይም ባዮሜትሪክ ዳታን፣

(ሐ) የአካላዊ ወይም የአዕምሯዊ ጤንነት ወይም ሁኔታን፣

(መ) የወሲባዊ ሕይወትን፣

(ሠ) የፖለቲካ አመለካከትን፣

(ረ) የሙያ ማኅበር አባልነትን፣

(ሰ) ሃይማኖትን ወይም ሌላ ሃይማኖት ነክ አስተሳሰብን፣

(ሸ) የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀልን፤

(ቀ) የተፈጸመ ወይም ተፈጸመ የተባለ ወንጀልን አስመልክቶ የተካሄዱ ሂደቶችን፣ እነዚህ ሂደቶች የተጠናቀቁበት መደምደሚያን ወይም በሂደቶቹ ዙሪያ ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔን፣ ወይም

(በ) ኮሚሽኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ነው በማለት የሚወስነው ሌላ የግል ዳታን የተመለከተ ኢንፎርሜሽን ነው፤

(29) “የሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል” ማለት ከኢትዮጵያ ሌላ አገር፣ እንደዚሁም በዓለም አቀፍ ሕግ የሚተዳደር ዓለም አቀፍ ተቋምና የተቋሙ ቅርንጫፍ አካላት፣ ወይም በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ አገራት መካከል በተደረገ ስምምነት የተቋቋመ ተቋም ነው፤

(30) “ትራፊክ ዳታ” ማለት በኮምፒውተር ሥርዓት ከሚደረግ ኮምኒኬሽን ጋር የተያያዘ፤ እና በኮምኒኬሽኑ ሠንሠለት ውስጥ ባሉ ሥርዓቶች የሚመነጭና የኮምኒኬሽን መነሻን፣ መድረሻን፣ የጉዞ መስመርን፣ ጊዜን፣ ቀንን፣ መጠንን፣ ክፍለ ጊዜን፣ ወይም የአገልግሎቱን ዓይነትን የሚገልጽ ማንኛውም ዳታ ነው፤ እንደዚሁም

(31) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

3. **<u>የአዋጁ ዓላማ</u>**

የዚህ አዋጅ ዓላማ ማንኛውም ግለሰብ፤ ዜግነቱና የመኖሪያ አድራሻው ግምት ውስጥ ሳይገባ፤ መብቶቹ እና መሠረታዊ ነጻነቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ መከበራቸውን በተለይም ከእርሱ ጋር ተያያዥ የሆነው የግል ዳታ በአውቶሜትድ መንገድ ሲቀናበር የግላዊነት መብቱን ባከበረ መልኩ መካሄዱን ማረጋገጥ ነው።

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

(1) ይህ አዋጅ በሙሉ ወይም በከፊል አውቶሜትድ በሆነ፣ እንደዚሁም የመዝገብ ሥርዓት አካል የሆነ ወይም የመዝገብ ሥርዓት አካል እንዲሆን የታሰበና አውቶሜትድ ባልሆነ በሌላ መንገድ በሚደረግ የግል ዳታ ማቀናበር ላይ ተፈጻሚ ነው።

(2) ከዚህ በተቃራኒ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ይህ አዋጅ ማንኛውንም የግል ዳታ በተመለከተ በዳታ ተቆጣጣሪ ወይም በዳታ አቀናባሪ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው፤

(ሀ) የተቋቋመው በኢትዮጵያ ከሆነና ዳታው የተቀናበረው ድርጅቱ ከተቋቋመበት አውድ አንፃር፣

(ለ) የተቋቋመው በኢትዮጵያ ባይሆንም ዳታው በኢትዮጵያ አልፎ ለመሻገር ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ መሳሪያን በመጠቀም የሚቀናበር፣ ወይም

(ሐ) የሚቀናበረው ዳታ በከፊል ወይም በሙሉ ከኢትዮጵያ የመነጨ

ከሆነ ብቻ ነው።

(3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) ላይ የተመለከቱት የዳታ ተቆጣጣሪና የዳታ አቀናባሪ ለዚህ አዋጅ ዓላማ መቀመጫውን በኢትዮጵያ ያደረገ ወኪል ሊኖራቸው ይገባል።

(4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) ላይ ለተመለከተው ድንጋጌ ዓላማ

(ሀ) መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ የሆነ ግለሰብ፣

(ለ) በፌዴራል ወይም በክልል ሕግ የተቋቋመ ተቋም፣ እና

(ሐ) በፊደል (ሀ) ወይም (ለ) በተጠቀሰው ውስጥ የማይወድቅ ነገር ግን በኢትዮጵያ ቢሮ ወይም ቅርንጫፍ በመክፈት ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሥራውን የሚፈጽም ወይም በመደበኛነት የሚያከናውን ሰው

በኢትዮጵያ የተቋቋመ ተብሎ ይገመታል።

(5) ይህ አዋጅ በሚከተሉት ማለትም

(ሀ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ላይ የተጣሉ ገደቦች ተብለው በተለዩ የግል ዳታ ማቀናበሮች፣ እና

https://chilot.me



(ለ) ከውጭ አገራት በመነጨ እና በኢትዮጵያ አልፈው ወደ ሶስተኛ አገራት የሚሻገሩ የግል ዳታ ማቀናበሮች

ላይ ተፈፃሚነት አይሆንም።

## ምዕራፍ ሁለት
## የኢትዮጵያ የግል ዳታ ጥበቃ ኮሚሽን

### 5. መቋቋም

የኢትዮጵያ የዳታ ጥበቃ ኮሚሽን የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፤ ተጠሪነቱም ለምክር ቤቱ ነው።

### 6. የኮሚሽኑ ሥልጣን እና ተግባራት

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፤

(1) የዚህ አዋጅ ተፈጻሚነትን ያረጋግጣል፣

(2) ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው አስፈላጊውን አስተዳደራዊ መዋቅር ይፈጥራል፣

(3) ይህን አዋጅ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎች፣ አመላካች መመሪያዎች እና ቅጾች ያወጣል፣

(4) ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

(5) ሕብረተሰቡ በዚህ አዋጅ ኮሚሽኑ ያሉትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲያውቁ፣ ዳታ ባለቤቶች ያሏቸውን መብቶች እንዲያውቁና እነዚህን መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩ፣ ዳታ ተቆጣጣሪዎች እና ዳታ አቀናባሪዎች ያሉባቸውን ግዴታዎች እንዲያውቁ፣ እንደዚሁም በዚህ አዋጅ ውስጥ በሚወድቁ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣

(6) ግለሰቦችን ጨምሮ የዳታ ተቆጣጣሪዎች የያዟቸው የግል ዳታ በዳታ ጥበቃ መርሆዎች መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ያደርጋል፣

(7) የግል ዳታና ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ አጠቃቀምን በሚመለከት ቁጥጥር ያካሂዳል፣ ያገኘውንም ውጤት ከአስተያየት ጋር በየጊዜው ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

(8) በውስጣቸው የግል ዳታ ማቀናበርን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ ረቂቅ ሕጎችንና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በተመለከተ ምክረ ሃሳብ ይሰጣል፤

(9) የግለሰቦችን የግላዊነት መብት ላይ ተጽዕኖ በሚያስከትሉ ጉዳዮች ዙሪያ የሕብረተሰቡን ተወካዮችና ተቋሞች ይጋብዛል፣ ያወያያል፣ ከእነዚህም ጋር በጋራ ይሠራል፣

(10) ሲጠየቅም ሆነ በራሱ ተነሳሽነት የዚህ አዋጅ አተገባበርን በተመለከተ ለማንኛውም ሰው ምክር ይሰጣል፤

(11) የዳታ ማቀናበርና የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ በግላዊነት መብት ላይ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ አነስተኛ እንዲሆን በማድረግ ዙሪያ ጥናቶችን ያጠናል፣ ዕድገቱን ይከታተላል፤ የጥናት እና የክትትል ውጤቱንም ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፣

(12) በሰዎች የግላዊነት መብት ዙሪያ ያሉ ዓለማቀፋዊ ስምምነቶችን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በመቀበሏ አስፈላጊነት ዙሪያ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፣

(13) ቅሬታዎች ሲቀርቡለት ሕጋዊ የምርመራ ሂደቶችንና መርሆዎችን በመከተል ይመረምራል፣ ለምርመራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባል፤

(14) የዳታ ተቆጣጣሪዎችንና የዳታ አቀናባሪዎችን መዝገብ ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤

(15) ዳታ ሊጠፋ ወይም ይዘቱ ሊቀየር ይችላል ብሎ በበቂ ምክንያት ሲጠረጥር፣ የትራፊክ ዳታን ጨምሮ ዳታውን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ይጠይቃል፤

(16) ዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ዳታ አቀናባሪው ይህንን አዋጅ ተላልፏል፣ በመተላለፍ ላይ ነው፣ ወይም ሊተላለፍ ነው ብሎ ሲያምን ይህን ለማስቆም ትዕዛዝ ይሰጣል፤

(17) በዚህ አዋጅ ላይ የተቀመጡትን ግዴታዎቹን ለመወጣት ከሌሎች አገራት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች ጋር፤ በተለይም ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ አግባብነት ያላቸውን ኢንፎርሜሽኖች በመለዋወጥ በትብብር ይሠራል፤ እንደዚሁም

(18) በዚህ አዋጅ፣ ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በወጡ ሌሎች ሕጎች ወይም በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነት ይተገብራል።

## 7. የኤጀንሲው አቋም

ኤጀንሲው፡-

(1) ኮሚሽነር፣

(2) ሶስት ምክትል ኮሚሽነሮች፣ እና

(3) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 8. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ፤ ምክር ቤቱ በሚወስነው በማናቸውም የኢትዮጵያ ክልሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

## 9. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በምክር ቤቱ ይመደባል።

## 10. የሒሳብ መዛግብት

(1) ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት መያዝ አለበት።

(2) የኮሚሽኑ የሒሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## 11. አሿሿምና ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች

(1) ኮሚሽነሩና ምክትል ኮሚሽነሮቹ በምክር ቤቱ ይሾማሉ።

(2) የኮሚሽነሩ የሥራ ዘመን ስድስት፤ የምክትል ኮሚሽነሮቹ የሥራ ዘመን አራት ዓመት ነው።

(3) ማንኛውም ሰው

(ሀ) ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ተገዥ የሆነ፤

(ለ) ለሰብዓዊ መብት መከበር ተቆርቋሪ የሆነ፤

(ሐ) በሕግ፤ በዳታ ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ፣ ወይም በልምድ ሰፊ ዕውቀት ያካበተ፤

(ሠ) በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ እና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

(ረ) በወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፤
(ሰ) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤
(ሸ) ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፤ እንደዚሁም
(ቀ) ዕድሜው ከ35 ዓመት በላይ የሆነ
ሊሾም ይችላል።

12. ተሿሚ ከኃላፊነት የሚነሳበት ምክንያቶች

(1) አንድ ተሿሚ
(ሀ) ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግና ይህንንም በተመለከተ ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ በፅሁፍ ሲሰጥ፤
(ለ) በሕመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤
(ሐ) በከባድ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ ከሆነ፤
(መ) ግልጽ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፤ ወይም
(ሠ) የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ
እንዳግባብነቱ ከኃላፊነት ይነሳል፤ ወይም ሹመቱ ቀሪ ይሆናል።
(2) አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከኃላፊነት ከተነሳበት ወይም ሹመቱ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት በስድስት ወራት ውስጥ በሌላ ተሿሚ መተካት አለበት።
(3) አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል (ለ) እስከ (መ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሠረት ከኃላፊነቱ የሚነሳው ጉዳዩ ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ልዩ አጣሪ ጉባዔ ከተመረመረ በኋላ ነው።
(4) በልዩ አጣሪ ጉባዔ በአብላጫ ድምጽ ተደግፎ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ምክር ቤቱ መርምሮ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ተሿሚው ከኋላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።

13. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት

(1) ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ነው፤ ኃላፊነቱን በሙሉ ነጻነትና ያለአድልዎ ይፈጽማል፤ ለዚህም ከማንኛውም አካል ትዕዛዝ አይጠይቅም፤ አይቀበልምም።
(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚሽነሩ
(ሀ) በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
(ለ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤
(ሐ) በተፈቀደው የኮሚሽኑ የሥራ ዕቅድና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
(መ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ኮሚሽኑን ይወክላል፤
(ሠ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀምና የሒሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ እንደዚሁም
(ረ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በልዩ ሁኔታ በሚጸድቅ ደንብ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።

14. የምክትል ኮሚሽነሮቹ ሥልጣንና ተግባራት

(1) ምክትል ኮሚሽነሮቹን የሚሾሙት በምክር ቤቱ ሲሆን፤ ተጠሪነታቸው ለኮሚሽነሩ ነው።
(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምክትል ኮሚሽነሮቹ
(ሀ) የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳሉ፤

https://chilot.me



(ለ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜና ለዚህም ውክልና ሲሰጣቸው፣ ለኮሚሽነሩ የተሰጡትን ሥራዎች ያከናውናሉ፤ እንደዚሁም

(ሐ) ኮሚሽነሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ።

**15. ቃለ መሃላ እና ሚስጥራዊነት**

(1) ኮሚሽነሩና ምክትል ኮሚሽነሮቹ ሲሰየሙ ቃለ መሃላ መፈጸም አለባቸው።

(2) ኮሚሽነር፣ ምክትል ኮሚሽነር፣ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ወይም የኮሚሽኑ ወኪል የሆነ ወይም የነበረ ሰው

(ሀ) ይህ አዋጅ ወይም ሌሎች አዋጆች በሚፈቅዱት፣ ወይም

(ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ

መሠረት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ መሠረት ካለው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ጋር ተያይዞ ያገኘውን ማንኛውንም ዳታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መጠቀም ወይም ለሌላ ሰው ማሳወቅ የተከለከለ ነው።

(3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌን የተላለፈ ሰው ወንጀል ፈጽሟል፣ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥም በ50ሺ ብር ቅጣት ወይም እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እሥራት፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

## ምዕራፍ ሶስት
## የግል ዳታን ማቀናበር

**16. የሕጋዊነት መርሕ**

(1) የግል ዳታ ለማቀናበር ሕጋዊ ምክንያት መኖር አለበት። በተለይም የግል ዳታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3)፣ እንደዚሁም ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ደግሞ በአንቀጽ 18 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር ሊቀናበር አይገባም።

(2) የግል ዳታ ማቀናበር ሕጋዊ ነው የሚባለው

(ሀ) የዳታው ባለቤት ፈቃዱን የገለጸ፤

(ለ) ማቀናበሩ አስፈላጊና ከዳታ ባለቤቱ ጋር የተገባን ውል ከመፈጸም ጋር የተገናኘ፣ ወይም የዳታ ባለቤቱ ውል ከመግባቱ በፊት በጠየቀው መሠረት እርምጃዎችን ለመውሰድ ማቀናበርሩ አስፈላጊ፤

(ሐ) ማቀናበሩ የዳታ ተቆጣጣሪው ያለበትን ግዴታ ለመወጣት አስፈላጊ፤

(መ) ማቀናበሩ የዳታ ባለቤቱን ሕይወትና ጤናን ጨምሮ ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ አስፈላጊ፤

(ሠ) ማቀናበሩ ለብሔራዊ አደጋ ምላሽ ለመስጠት፣ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማክበር፣ ወይም መንግሥታዊ ተቋሞች የግል ዳታ ማቀናበርን ጨምሮ ሌሎች ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣት አስፈላጊ፤ ወይም

(ረ) ማቀናበሩ ለዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ዳታው ይፋ ለተደረገላቸው ሶስተኛ ወገኖች ሕጋዊ ጥቅሞች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና፤ እነዚህ ጥቅሞች የግል ዳታ ጥበቃ በሚያስፈልጋቸው የዳታ ባለቤቱ ሌሎች መሠረታዊ መብቶች የማይገደቡ

ከሆነ ነው።

(3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ረ) ተግባራዊ የሚሆነው በተለይ የዳታ ባለቤቱ ሕፃን ከሆነ ነው።



Weshare Laws

(4) የዳታ ማቀናበር ከሚከተለው ሕጋዊ ዓላማ ጋር ተመጣጣኝ፣ እንደዚሁም በየደረጃው የሚደረግ የማቀናበር ሥራ የተለያዩ የመንግሥትንና የግለሰብ ፍላጎቶችን እና መብቶችና ነጻነቶች አስመልክቶ ሚዛናዊነቱን በበቂ ሁኔታ ማሳየት አለበት።

## 17. የፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎች

(1) ለአንቀጽ 16(2)(ሀ) አፈጻጸም የግል ዳታ ማቀናበር የሚቻለው ማቀናበሩ ከመጀመሩ በፊት በዳታ ባለቤቱ በሚሰጥ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ ነው።

(2) የዳታ ባለቤቱ የሰጠው ፈቃድ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ፈቃዱ በነፃነት፣ በመረጃ ላይ በመመስረት፣ በግልጽ እና ሊነሳ የሚችል ሆኖ የተሰጠ መሆን አለበት።

(3) ዳታ ተቆጣጣሪው የዕቃዎችንና የአገልግሎቶችን አቅርቦት፣ ወይም የጥራት ደረጃቸውን፤ የውል አፈጻጸምን፣ ወይም የመብት አፈጻጸምን ከዚህ ዓላማ ጋር ተያያዥ ካልሆነና የግል ዳታን ለማቀናበር ከሚሰጥ ፈቃድ ጋር ማቆራኘት የለበትም።

(4) የዳታ ባለቤቱ ዳታ እንዲቀናበር ፈቃድ የሰጠው በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መሆኑን የማስረዳት ሸክም በዳታ ተቆጣጣሪው ላይ ያርፋል።

(5) የዳታ ባለቤቱ ለውል አፈጻጸም ዓላማ ሲባል የግል ዳታው እንዲቀናበር ሰጥቶ የነበረውን ፈቃድ ሲያነሳ፤ ፈቃድ በመነሳቱ ምክንያት ለሚመጣው ሕጋዊ ውጤት ኃላፊ ነው። ፈቃድ መነሳቱ ፈቃድ በነበረበት ጊዜ የተደረገው ማቀናበር ሕጋዊነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የለውም።

## 18. ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታን ማቀናበር

(1) ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ማቀናበር ክልክል ነው።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣

(ሀ) የዳታ ባለቤቱ ዳታው ከመቀናበሩ በፊት ለተጠቀሰው ዓላማ ፈቃዱን በጽሑፍ የሰጠ ከሆነ፣

(ለ) የማቀናበሩ ሥራ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ መዋል ከጀመረ በኃላ በወጡ ሕጎች የተደነገገ ከሆነ፣

(ሐ) ማቀናበሩ የዳታው ባለቤትን ወይም የሌላ ሰው ሕይወትንና ጤናን ለመጠበቅ አስፈላጊ ከሆነ፣ እና የዳታው ባለቤት ዳታው ከመቀናበሩ በፊት በሕግም ሆነ በአካል ስምምነቱን መግለጽ የማይችል ከሆነ፣

(መ) ማቀናበሩ የመንግሥታዊ ድርጅቶች ሕጋዊ የሆኑና ንግድ ነክ ያልሆኑ ዓላማዎችን ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነ፣

(ሠ) ማቀናበሩ ለሕክምና ዓላማዎች አስፈላጊ ከሆነ፣ በሕክምና ተቋም ከተከናወነ፣ እንዲሁም ለግል ዳታው በቂ የጥበቃ ደረጃ መኖሩ ከተረጋገጠለት፣ ወይም

(ረ) ማቀናበሩ በፍርድ ሂደት ላይ ወይም በሌሎች የመንግሥት ተቋማት ዚንድ ቀርበው ያሉ የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ሕጋዊ መብቶችን እና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆነን የግል ዳታ የሚመለከት ከሆነ

ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታን ማቀናበር ይፈቀዳል።

(3) ዘርን ወይም ጎሳን የተመለከተ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ማቀናበርን አስመልክቶ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም።

(4) የዳታ ባለቤቱ ሃይማኖትን ወይም ሌላ ሃይማኖት ነክ አስተሳሰብን የተመለከተ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ሊቀናበር የሚችለው፣

(ሀ) ማቀናበሩ በመንፈሳዊ ወይም በሃይማኖታዊ ድርጅት ወይም በድርጅቱ ቅርንጫፍ የሚደረግ ከሆነ፣ እንደዚሁም ማቀናበሩ ተፈጻሚ የሚሆነው በድርጅቱ አባላት በሆኑ ሰዎች ላይ፣ ወይም

(ለ) ማቀናበሩ በሃይማኖታዊ ወይም ሃይማኖት ነክ መርሆዎች ላይ በተመሠረተ ተቋም የሚካሄድ፣ እንደዚሁም ማቀናበሩ የሚካሄደው በተቋሙ አባላት፣ ሠራተኞች ወይም ሌሎች የተቋሙ አካላት በሆኑ ግለሰቦች፣ እና የተቋሙን ዓላማዎችና መርሆዎች ለማሳካት አስፈላጊ

ከሆነ ነው፡፡

(5) የልጆች የግል መረጃ ማቀናበር በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ይከናወናል፡፡

## 19. ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ተጨማሪ ምድቦች

(1) ኮሚሽኑ ተጨማሪ የግል ዳታ ምድቦችን ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ በማለት መመደብ ይችላል፡፡

(2) የግል ዳታ ምድቦች በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ተብለው በሚመደቡበት ጊዜ፣ ኮሚሽኑ

(ሀ) በዚህ ምድብ ውስጥ የተካተተ የግል ዳታ ማቀናበር በዳታው ባለቤት ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን የአደጋ የሥጋት ደረጃ፣

(ለ) በዚህ ምድብ ውስጥ የተካተተ የግል ዳታ የሚጠበቅበትን የሚስጥራዊነት ደረጃ፣

(ሐ) በዚህ ምድብ የተካተተ ዳታ ማቀናበሩ በቁጥር ከፍ ባሉና በሚታወቁ የዳታ ባለቤቶች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የአደጋ የሥጋት ደረጃ፣ እና

(መ) መደበኛ የሆኑ የግል ዳታ ድንጋጌዎች የሚሰጡት ጥበቃ በቂ መሆናቸውን

መነሻ በማድረግ በዚህ ሥር የተካተቱ የግል ዳታዎች የሚቀናበሩበትን ተጨማሪ ምክንያቶች መወሰን ይችላል፡፡

(3) ኮሚሽኑ ተጨማሪ የደህንነት እርምጃዎችን ወይም ገደቦችን የሚጠይቁ ሌሎች የግል የዳታ ምድቦችን በተመለከተ መወሰን ይችላል፡፡

## 20. የሕጻን ልጅ የግል ዳታን ማቀናበር

(1) የሕጻን ልጅ የግል ዳታ ማቀናበር የሕጻኑን ልጅ መብትና ጥቅም በሚጠቅም እና በሚያስቀድም መንገድ መከናወን አለበት፡፡

(2) የሕጻን ልጅ የግል ዳታ የማቀናበር ሂደት ሕጋዊ የሚሆነው

(ሀ) ወላጅ ወይም አሳዳጊ ፈቃድ ወይም ሥልጣን የሰጠ፣ ወይም

(ለ) ማቀናበሩ ለሕጻኑ ወሳኝና አስፈላጊ ጥቅሞች አስፈላጊ

ከሆነ ነው፡፡

(3) የዳታ ተቆጣጣሪው በወቅቱ ያለውን ቴክኖሎጂ ግምት ውስጥ በማስገባት የዳታ ባለቤቱን ዕድሜ፣ እንዲሁም ፈቃድ በልጁ ወላጅ ወይም ሞግዚት የተሰጠ መሆኑን ለማጣራት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

(4) የንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ስለ ውል አመሠራረት፣ ውጤት ወይም የጸና ስለመሆኑ በውል ሕጎች የተደነገገውን አያፈርስም፡፡

## 21. የርዕታዊነት እና የግልጽነት መርሕ

(1) የግል ዳታ ማቀናበር በርዕታዊነት እና በግልጽነት መርሕ ላይ መመሥረት አለበት፡፡

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠውን ድንጋጌ ለማሟላት፣

(ሀ) የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው የዳታ ማቀናበሩን በተመለከተ ለዳታ ባለቤቱ በተለይም ለሕጻን ልጅ ኢንፎርሜሽን ለመስጠት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፤ ይህ ኢንፎርሜሽን ለመረዳት የማይከብድ ቋንቋን በመጠቀም የተከናወነና አጭር፣ ግልጽ፣ በቀላሉ የሚነበብና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ ቅርጽን ጥቅም ላይ ያዋለ መሆን አለበት፤

(ለ) ማቀናበሩ የዳታ ባለቤቱን ያላግባብ በማይጎዳ፣ ባልጠበቀውና በማያሳስት ሁኔታ ያልተከናወነ፤ ወይም

(ሐ) ማቀናበሩ የዳታ ባለቤቱን መረጃ የማግኘት መብት የሚያከብር፣ እንደዚሁም ግልጽ፣ ክፍት እና ተኣማኒ በሆነ መልኩ የተከናወነ

መሆን አለበት።

(3) ዳታ ተቆጣጣሪው በአንቀጽ 35 የተዘረዘሩትን ኢንፎርሜሽኖችን የመስጠት የዘወትር ግዴታ አለበት።

## 22. <u>የዓላማ ገደብ መርሕ</u>

(1) የግል ዳታ መሰብሰብ የሚቻለው ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆነ፤ እንደዚሁም ለተገለጸ፣ ለታወቀ እና ሕጋዊ ለሆነ ዓላማ ወይም ዓላማዎች ነው።

(2) የግል ዳታ ከዚህ ዓላማ ወይም ከእነዚህ ዓላማዎች ጋር በማይጣጣም መልኩ በቀጣይ ማቀናበር አይቻልም።

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ ለተቀመጡት መርሆዎች አተገባበር፤ የግል ዳታ የተሰበሰበበት ዓላማ

(ሀ) የዳታ ተቆጣጣሪው ለዳታ ባለቤቱ በሚሰጠው ማስታወቂያ፣ ወይም

(ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45(4)(ሠ) መሠረት ለኮሚሽኑ በሚሰጥ ማስታወቂያ መሠረት

መገለጽ አለበት።

(4) የግል ዳታ ይፋ የተደረገበት አግባብ ዳታው ከተሰበሰበበት ዓላማ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለመወሰን፤

(ሀ) የግል ዳታ ይፋ የተደረገላቸው ሰዎች ዳታ የሚያቀናብሩበት ዓላማ፣ እና

(ለ) የግል ዳታ የሚያቀናብረው ሰው የተጣለበት ኃላፊነት ወይም የሚያከናውናቸው ተግባራትን

መመልከት ያስፈልጋል።

(5) ለንዑስ አንቀጽ (4) አፈጻጸም ለሕብረተሰብ ጥቅም የሚደረግ የወመዘክር፣ ለሳይንሳዊና ታሪካዊ፣ እንደዚሁም ለስታቲስቲክስ ዓላማዎች የሚደረጉ ቀጣይ ማቀናበር ከእነዚህ ዓላማዎች ጋር የሚጣጣሙ የደህንነት እርምጃዎችን ማካተት አለበት።

## 23. <u>የዳታ ልከኝነት መርሕ</u>

የግል ዳታ ከሚቀናበርበት ዓላማ ወይም ዓላማዎች አንጻር በቂ፣ አግባብነት ያለውና መጠኑ ያላለፈ መሆን አለበት።

## 24. <u>የትክክለኛነት መርሕ</u>

(1) የግል ዳታ ትክክለኛ እና እንዳስፈላጊነቱ ወቅታዊ መሆን አለበት።

(2) የግል ዳታ በውስጡ የዳታ ባለቤቱ ወይም ሶስተኛ ወገን የሰጠውን ኢንፎርሜሽን በትክክል መዝግቦ እስከያዘ ድረስ

(ሀ) በተለይም ዳታው የተሰበሰበትን እና በቀጣይ የተቀናበረበት ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን የወሰደ፣ እንደዚሁም

(ለ) የዳታ ባለቤቱ ዳታው ትክክለኛ አለመሆኑን ለዳታ ተቆጣጣሪው ገልጾ ከሆነና የዳታ ባለቤቱ አስተያየት ተካቶ

ከሆነ ትክክለኛ ያልሆነ ኢንፎርሜሽን ማካተቱ የትክክለኛነት መርሕን ጥሷል አያስብልም፡፡

**25.** **የክምችት ገደብ መርሕ**

(1) ለማንኛውም ዓላማ ወይም ዓላማዎች የተቀናበረ የግል ዳታ ለዓላማው ወይም ለዓላማዎቹ አስፈላጊ ከሆነ ጊዜ በላይ ሊከማች አይገባም፡፡

(2) የሪከርዱ ክምችት

(ሀ) በዚህ ወይም በሌላ አዋጅ አስፈላጊ ወይም የተፈቀደ ነው በማለት የተደነገገ ከሆነ፣

(ለ) ከኃላፊነትና ከተግባር አንጻር ለሕጋዊ ዓላማ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣

(ሐ) የዳታ ባለቤቱ ፈቃድ የሰጠበት ከሆነ፣

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

(3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለታሪክ፣ ለስታቲስቲክስ እና ለምርምር ዓላማ ታስቦ የተቀመጠ የግል ዳታ ላይ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

(4) የግል ዳታን ለታሪክ፣ ለስታስቲክስ እና ለምርምር ዓላማ የሚያስቀምጥ ሰው የግል ዳታን የያዙ ሪከርዶች ላልተፈቀዱ ዓላማዎች ይፋ እንዳይደረጉ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ለማድረግ በቂ ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(5) የዳታ ባለቤቱን የግል ዳታ ሪከርድ በመጠቀም የዳታ ባለቤቱን የሚመለከት ውሳኔ የሚወስን ሰው፤

(ሀ) ሪከርዱን በሕግ ወይም በአሠራር ደንብ ለተቀመጠው ጊዜ ያህል፣ ወይም

(ለ) ዳታ ማቆየት የሚቻልበትን የጊዜ ርዝማኔ የሚወስን ሕግ ወይም የአሠራር ደንብ የሌለ እንደሆነ፣ የዳታ ባለቤቱ ሪከርዱን ለመመርመር ዕድል እንዲያገኝ ጣያቄ ለማቅረብ ለሚያስችል የጊዜ ርዝማኔ ያህል

ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

**26.** **የምሉዕነት እና የሚስጥራዊነት መርሕ**

(1) በሥራቸው አጋጣሚ የግል ዳታ የሚያገኙ ሠራተኞቹን ታማኝነት ለማረጋገጥ የዳታ ተቆጣጣሪው አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

(2) የግል ዳታ ማቀናበሩ በዳታ ተቆጣጣሪው ምትክ በዳታ አቀናባሪው የሚከናወን ከሆነ፣ ይህን መርሕ ለማክበር ዳታ ተቆጣጣሪው

(ሀ) የሚከናወነውን የማቀናበር ሥራ ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክና ተቋማዊ የደህንነት እርምጃዎች ያሉትና ለዚህም ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል የዳታ አቀናባሪ መምረጥ፣ እንደዚሁም

(ለ) እነዚህ እርምጃዎች መተግበራቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ መውሰድ

አለበት፡፡

(3) የግል ዳታ ማቀናበሩ በዳታ ተቆጣጣሪው ምትክ ሆኖ በዳታ አቀናባሪው የተከናወነና

(ሀ) ማቀናበሩ በውል ወይም በፅሁፍ በተደገፈ ማስረጃ ያልተከናወነ፣

(ለ) የዳታ አቀናባሪው ሥራውን በዳታ ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ መሠረት ብቻ ማከናወን፣ እና

(ሐ) ውሉ የምሉዕነትና የሚስጥራዊነት መርሕ በዳታ ተቆጣጣሪው ላይ ከጣለበት ግዴታ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ግዴታን በዳታ አቀናባሪው ላይ የማይጥል

ከሆነ፣ ዳታ ተቆጣጣሪው የምልዑነትና የሚስጥራዊነት መርሕን እንዳከበረ አይቆጠርም፡፡

(4) ዳታ ተቆጣጣሪውና ዳታ አቀናባሪው በሥልጣናቸው ሥር ያለና በሥራው ኢጋጣሚ የግል ዳታን ማግኘት የሚችል ግለሰብን በተመለከተ፣ ይህ ግለሰብ በሕግ ካልተገደደ በስተቀር ከዳታ ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ ውጪ የግል ዳታን አለማቀናበሩን ለማረጋገጥ ተገቢውን ዕርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።

**27. <u>የደህንነት መርሕ</u>**

(1) ያልተፈቀደና ሕጋዊ ያልሆነ የግል ዳታ ማቀናበርን እንደዚሁም የግል ዳታ ድንገተኛ መጥፋትን ወይም መውደምን ወይም መጎዳትን ለማስቀረት ተገቢውን የሆነ የቴክኒክና ተቋማዊ እርምጃዎች መወሰድ አለበት።

(2) የምሉዕነት እና የሚስጥራዊነት መርሕን ለመተግበር የቴክኖሎጂ ዕድገትንና ይህን ለመተግበር የሚጠይቀው ወጪን ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተቀመጠ እርምጃ

(ሀ) ካልተፈቀደ ወይም ሕጋዊ ካልሆነ ማቀናበር፣ ወይም በድንገተኛ የዳታ መጥፋት፣ መውደም ወይም መጎዳት ምክንያት ሊደርስ ከሚችል ጥፋት፣ እና

(ለ) ጥበቃ ከሚደረግለት የዳታ ባህርይ

ጋር የሚመጣጠን የደህንነት ደረጃዎችን ማረጋገጥ አለበት።

(4) የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃን፣ ይህን ለመተግበር የሚያስፈልግ ወጪን፣ እና የማቀናበሩን ባሕርይ፣ ወሰን፣ ዓውድ፣ እና ዓላማዎች፤ እንደዚሁም በግለሰቦች ነጻነቶችና መብቶች ላይ ሊያመጣ የሚችለውን የአደጋ ሥጋትና መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ የዳታ ተቆጣጣሪውና የዳታ አቀናባሪው

(ሀ) ግላዊ ዳታን በተመለከተ ምናባዊ ስም መጠቀምንና ዳታውን መመስጠርን፤

(ለ) የማቀናበሩን ሥርዓቶችና አገልግሎቶች ምስጢራዊነት፣ ምሉዑነት፣ ተገልጋዩ በቀላሉ የሚያገኘው መሆኑን እና አደጋ የመቋቋም ብቃትን፤

(ሐ) አካላዊና ቴክኒካዊ ተግዳሮቶች በሚያጋጥሙበት ወቅት ተገልጋዩ የግል ዳታን እንደገና በፍጥነት እንዲያገኘውና ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ብቃትን፣ እንደዚሁም

(መ) የማቀናበሩን ደህንነት ለማረጋገጥና የቴክኒክና ተቋማዊ ዕርምጃዎችን ውጤታማነት ለመገምገም የሚደረጉ መደበኛ የሙከራ፣ የምዘናና የግምገማ ሂደቶችን

ጨምሮ ተገቢ የሆነ የቴክኒክና ተቋማዊ እርምጃዎችን በመተግበር ለሥጋቱ ደረጃውን የሚመጥን የደህንንነት ደረጃ ማረጋገጥ አለባቸው።

(5) ተገቢውን የደህነነት ደረጃ ለመመዘን በዋነኛነት በማቀናበሩ ላይ ያሉ ሥጋቶች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

(6) በማስተላለፍ ሂደት፣ በክምችት ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ እየተቀናበረ ያለ የግል ዳታ ባልታሰበ ወይም ሕጋዊ ባልሆነ አግባብ መውደም፣ መጥፋት፣ ይዘት መቀየር፣ ይፋ መደረግ፣ ተደራሽ መደረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ሥጋት ተብሎ ይቆጠራል።

**28. <u>ዳታ የማስተላለፍ መርሕ</u>**

ከዳታ ማስተላለፍ ጋር ተያያዥ የሆኑና በቀጣይ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እንዲቀናበር ወደ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል የግል ዳታ የሚተላለፈው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን መሠረት ብቻ፤ እንደዚሁም ዳታው የሚተላለፍለት የሥልጣን ክልል ተገቢ የሆነ የጥበቃ ደረጃ የሚያደርግ መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

**29. <u>በሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል ውስጥ ያለ የጥበቃ ደረጃ</u>**

(1) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 28 መሠረት ተገቢ የሆነ የጥበቃ ደረጃ የሚመዘነው በዳታ ማስተላለፉ ተግባር ወይም ተግባራቶች ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

(2) ለንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም፣ የዳታው ባህርይ፣ የታሰበው የማቀናበር ዓላማ፣ ማቀናበሩ ሊወስድ የሚችለው ጊዜ፣ የዳታው መነሻ እና መዳረሻ አገር፣ በሶስተኛው ወገን የሥልጣን ክልል ውስጥ ያለ የሕግ የበላይነት መርሕ አተገባበር፣ እንደዚሁም በሶስተኛው ወገን የሥልጣን ክልል ውስጥ የሚተገበሩ የሙያ እና የደህንነት እርምጃዎች በተለይ ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

(3) በሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል ውስጥ ተገቢ የሆነ የጥበቃ ደረጃ መኖሩን በተመለከተ ኮሚሽኑ ይወስናል፡፡

(4) ተገቢ የሆነ የጥበቃ ደረጃ ባይኖርም፣ በዚህ አዋጅ የዳታ ባለቤቱን የሙብት ጥሰቶች መገደብ በሚችል መልኩ የግል ዳታ እንዲተላለፍ ሲወስን፤ ኮሚሽኑ

(ሀ) የዳታ ባለቤቱ ዳታው ወደ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል እንዲተላለፍ ፈቃድ የሰጠ መሆኑን፣ እና

(ለ) በኮሚሽኑ ተቀባይነት ያገኘና ከግል ዳታው ውስጥ ተቆርጦ ወይም ተቀንሶ የወጣ ክፍል መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(5) በንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለግል ዳታ ተገቢ የሆነ የጥበቃ ደረጃ ወደማይሰጥ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል የግል ዳታን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

**30. <u>ዳታ ከአገር ወደ ውጪ የሚተላለፍባቸው ሁኔታዎች</u>**

(1) የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው የግል ዳታን ወደ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል ማስተላለፍ የሚችለው

(ሀ) የግል ዳታ ደህንነትንና ጥበቃን በሚመለከት ተገቢ የሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የወሰደ መሆኑን ለኮሚሽኑ ማስረጃ የሰጠ፣

(ለ) የዳታ ባለቤቱ ዳታ ከማስተላለፉ ጋር የተያያዙ ሥጋቶችን የተገለጹለት ከሆነና ይህን መነሻ በማድረግ ግልጽ የሆነ ፈቃድ የሰጠ፣

(ሐ) ማስተላለፉ አስፈላጊ፣ ወይም

(መ) ሕብረተሰቡ መረጃ እንዲያገኝ በሕግ የተደነገገና የተላለፈው መረጃ ከመዝገብ የተወሰደ

ከሆነ ነው፡፡

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) መሠረት

(ሀ) በዳታ ባለቤቱ እና በዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ዳታ አቀናባሪው መካከል የተደረገ ውልን ለመፈጸም፣ ወይም በዳታ ባለቤቱ ጥያቄ መሠረት ለሚደረግ የቅድመ ውል እርምጃዎች አስፈላጊ ከሆነ፣

(ለ) በዳታ ተቆጣጣሪው እና በሌላ ሰው መካከል ለዳታ ባለቤቱ ጥቅም ሲባል ውል ለመግባት ወይም ውል ለመፈጸም የሚደረግ ከሆነ፣

(ሐ) ለማንኛውም የሕዝብ ጥቅም ተብሎ የሚደረግ፣

(መ) ሕጋዊ መብትን ለማቋቋም፣ ለመፈጸም ወይም ለመከላከል የሚደረግ፣

(ሠ) የዳታው ባለቤት በአካል ወይም በሕጋዊ መንገድ ፈቃድ መስጠት በማይችልበት ጊዜ የዳታ ባለቤቱን ወይም የሌሎች ሰዎችን ወሳኝ ፍላጎቶች ለመጠበቅ፣ ወይም

(ረ) በዳታ ባለቤቱ ፍላጎቶች፣ መብቶች እና ነጻነቶች ጫና ሥር ያልወደቁ እና በዳታ ተቆጣጣሪው ወይም በዳታ አቀናባሪው ሕጋዊ ፍላጎቶች ምክንያት የሚደረግ ከሆነ

የዳታ ማስተላለፉ አስፈላጊ ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡

**31. ዳታ ከአገር ወደ ውጪ ሲተላለፍ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች**

(1) ኮሚሽኑ ዳታ ወደ ሶስተኛ አገር የሥልጣን ክልል የሚያስተላልፍ ሰው የዳታ ጥበቃ የደኅንነት እርምጃዎቹ ውጤታማ መሆናቸውን ወይም ማስተላለፉ የግድ እንደሆነ እንዲያሳይ መጠየቅ ይችላል።

(2) የዳታ ባለቤቶች መብቶችን እና መሠረታዊ ነፃነቶችን ለመጠበቅ ሲባል ኮሚሽኑ ማስተላለፉን ሊከለክል፣ ሊያቋርጥ ወይም ሌሎች አስፈላጊ ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ማዘዝ ይችላል።

**32 የዳታ ማዕከሎችና ሰርቨሮች**

(1) ኮሚሽኑ የመንግሥት ስትራቴጂካዊ ፍላጎቶች መሠረት በማድረግ፣ ወይም የመንግሥት ገቢን ከመጠበቅ አንጻር፣ የተወሰኑ የግል ዳታ ምድቦች ወሳኝ የግል ዳታ ናቸው በማለት ሊቀናበሩ የሚችሉት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ሰርቨር ወይም የዳታ ማዕከል ነው በማለት ገደብ ማስቀመጥ አለበት።

(2) ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታን ከአገር ወደ ውጪ ለማስተላለፍ በቅድሚያ የኮሚሽኑን ፈቃድ ማኘየት አለበት በድንበር ተሻጋሪ መልኩ ማቀናበር የተከለከለ ነው።

**33. የተጠያቂነት መርሕ**

(1) ዳታ ተቆጣጣሪውና እንዳግባብነቱ ዳታ አቀናባሪው በራሱ ወይም በምትኩ የሚከናወኑ ዳታ የማቀናበር ተግባራትን በተመለከተ በዚህ አዋጅ የተቀመጡት ግዴታዎችን የመወጣት ኃላፊነት አለበት።

(2) ዳታ ተቆጣጣሪው በራሱ ወይም በምትኩ የሚከናወኑ የማቀናበር ሥራዎች በዚህ አዋጅ መሠረት መከናወናቸውን ማሳየት አለበት።

## ምዕራፍ አራት
## የዳታ ባለቤቶች መብቶች

**34. የዳታ ባለቤት መብት መርሕ**

የግል ዳታ የሚቀናበረው በዚህ አዋጅ ውስጥ በተዘረዘሩ የዳታ ባለቤቱ መብቶች መሠረት ነው።

**35. መረጃ የማግኘት መብት**

(1) የግል ዳታ ከዳታ ባለቤቱ ወይም ከሌላ ምንጮች የተሰበሰበ ከሆነ፣ የዳታ ባለቤቱ

(ሀ) የዳታ ተቆጣጣሪውን ስም እና ሙሉ አድራሻን፣

(ለ) የዳታ ተቆጣጣሪው ተወካይ ስም እና ሙሉ አድራሻን፣

(ሐ) የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታ ጥበቃ መኮንን እና የተወካዩ ሙሉ አድራሻን፣

(መ) የማቀናበሩ ዓላማዎችን፣

(ሠ) ለጥያቄዎች መልስ መስጠት በፈቃደኝነት ወይም በግዴታ የተመሰረተ ስለ መሆኑና ምላሽ አለመስጠት የሚያስከትለው ውጤት መኖሩን፣

(ረ) የማቀናበር ሂደቱ ሕጋዊ መሠረትን፣

(ሰ) የግል ዳታው ተቀባዮች ወይም የተቀባዮች ምድቦችን፣

(ሸ) የግል ዳታው ለሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል የሚተላለፍበት ዝርዝር ኢንፎርሜሽንን፣

(ቀ) የግል መረጃው ተጠብቆ የሚቆይበት ጊዜን፣

(በ) የዳታ ባለቤቱ ዳታ ከማቀናበር አንጻር ያሉት መብቶችን፣
(ተ) ፈቃድን የማንሳት መብትን፣
(ቸ) ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አቤቱታን የማቅረብ መብትን፣
(ኀ) ፕሮፋይሊንግን ጨምሮ በአውቶሜትድ መሳሪያ የሚሰጥ ውሳኔ መኖርን፣
(ነ) የተቀናበረው ዳታ ምድቦችን፣ እና
(ኘ) ርዕታዊና ግልጽ ማቀናበር መኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን

በተመለከተ ከዳታ ተቆጣጣሪው ኢንፎርሜሽን የማግኘት መብት አለው፡፡

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) ሥር ከተዘረዘረው ኢንፎርሜሽን በተጨማሪ፣ የግል ዳታዎች የተሰበሰቡት በቀጥታ ከዳታው ባለቤት ካልሆነ፣ የዳታ ተቆጣጣሪው

(ሀ) የእነዚህ የግል ዳታ ምድቦችን፣ እና
(ለ) የግል ዳታው ምንጭን

በተመለከተ ለዳታ ባለቤቱ ኢንፎርሜሽን መስጠት አለበት፡፡

(3) የዳታ ባለቤቱ የግል ዳታዎች የተሰበሰቡት በቀጥታ ከዳታው ባለቤት ከሆነ፣ ዳታ ተቆጣጣሪው ለዳታ ባለቤቱ በንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘረውን ኢንፎርሜሽን የግል ዳታው በተሰበሰበበት ጊዜ ማሳወቅ አለበት፡፡

(4) የዳታ ባለቤቱ አግባብነት ያለውን ኢንፎርሜሽን ቀድሞ ያለው ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

(5) የግል ዳታ የተሰበሰበው ከዳታ ባለቤቱ ካልሆነና፣ ማቀናበሩ በሕግ የተደነገገ ከሆነ፣ ወይም ለዳታ ባለቤቱ ኢንፎርሜሽኑን መስጠቱ አዳጋች ከሆነ ወይም ተመጣጣኝ ያልሆነ ድካም የሚያስከትል ከሆነ፤ ዳታ ተቆጣጣሪው ኢንፎርሜሽኑን ለመስጠት አይገደድም፡፡

## 36. <u>የተደራሽነት መብት</u>

የዳታው ባለቤቱ ሲጠይቅና፣ ይህ ጥያቄ ተቀባይነት ባለው የጊዜ ልዩነት ውስጥ የቀረበ ከሆነ

(ሀ) ከእርሱ ጋር የተገናኘ የግል ዳታ መቀናበሩን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ፣
(ለ) የተቀናበረው ዳታ በሚነበብ ቅርጽ እንዲቀርብለት፣
(ሐ) የዳታ ምንጭን በተመለከተ ያለ ኢንፎርሜሽን በጠቅላላ፣
(መ) ዳታው የሚከማችበትን የጊዜ ርዝማኔ፣ እንደዚሁም
(ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት ግልጸኝነት ለማስፈን የዳታ ተቆጣጣሪው ማቅረብ ያለበትን ሌሎች ኢንፎርሜሽን

ከክፍያ ነጻና ያላግባብ መዘግየት የማግኘት መብት አለው፡፡

## 37. <u>የተደራሽነት መብት ቀሪ የሚሆንባቸው አግባቦች</u>

(1) የዳታ ተቆጣጣሪው

(ሀ) ይፋ መደረጉ የሌላ ግለሰብን ግላዊ መብት የሚጋፋ ሲሆን፣
(ለ) ዳታው ሕጋዊ ልዩ መብት ሥር የሚወድቅ ወይም የተገኘው በምርመራ ወይም በፍርድ ሂደት ከሆነ፣
(ሐ) የጤና ወይም የሕክምና ዳታ ከሆነና ዳታ ተቆጣጣሪው ዳታውን ተደራሽ ማድረጉ የሌላን ሰው ጤና ወይም ደህንነት ሊጎዳ ይችላል የሚል ግምት ካለው፣ ወይም
(መ) ለሥራ ቅጥር ተስማሚ የሆነን ተወዳዳሪ ለማጣራት፣ የመንግሥት ኮንትራት አሸናፊን ለመለየት እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለመስጠት የተሰበሰበና በዚህ ምክንያት ዳታው የግምገማ ወይም የአስተያየት

ይዘት ያለው ከሆነና የግል ዳታው ይፋ መደረግ በምስጢር መያዝ የነበረበትን የመረጃ ምንጭ የሚያጋልጥ ከሆነ

የግል ዳታ ለሚመለከተው ግለሰብ ተደራሽ እንዳይሆን መከልከል ይችላል።

(2) ዳታ ተቆጣጣሪው ጥያቄው ተደጋጋሚ ከመሆኑ ወይም ሥልታዊ ከመሆኑ ወይም ጥያቄዎቹ ይዘታቸው አሳማኝ ያልሆኑ ወይም ቅሬታ የሚያስከትሉ ከሆነና በዚህ ምክንያት ሥራውን የሚያስተጓጉል ከሆነ የዳታ ተቆጣጣሪው ጥያቄ አቅራቢው የግል ዳታ ተደራሽ እንዲደረግለት ያቀረበለትን ጥያቄ ወደ ጎን ሊተወው ይችላል።

## 38. <u>የማስተካከል መብት</u>

(1) የዳታ ባለቤት የግል ዳታው ትክክለኛ ያልሆነ፣ ያልተሟላ፣ አሳሳች፣ ወቅታዊ ያልሆነ፣ ወይም የሚቀናበረው ከዚህ አዋጅ በተቃራኒ ነው ብሎ በሚያምንበት ጊዜ፣ የዳታው ባለቤት ዳታው ያለ ምንም ክፍያና ያላግባብ መዘግየት እንዲስተካከል የዳታ ተቆጣጣሪውን የመጠየቅ መብት አለው።

(2) በዚህ ድንጋጌ መሠረት የግል ዳታ ከተስተካከለ፣ የዳታ ተቆጣጣሪው እርማቱ ከመጠየቁ በፊት ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ዳታው ተደራሽ ለተደረገለት ሰው የተደረገውን ማስተካከያ መግለጽ አለበት።

(3) በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የማስተካከያው ማስታወቂያ ሲደርሰው፣ የዳታ ተቆጣጣሪው በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር በሚገኝ መዝገብ ውስጥ ያለ ዳታን ማስተካከል አለበት።

## 39. <u>ማቀናበርን መደምሰስ</u>

(1) የዳታው ባለቤት

(ሀ) ከተሰበሰበበት ወይም ከተቀናበረበት ዓላማ አንጻር ሲፈተሽ ዳታው አስፈላጊ ካልሆነ፣

(ለ) የዳታ ባለቤቱ ዳታ እንዲቀናበር የሰጠውን ፈቃድ ካነሳና በቀጣይ ዳታ ለማቀናበር ሌላ ሕጋዊ መሠረት ከሌለ፣

(ሐ) የዳታ ባለቤቱ ዳታ የተቀናበረበትን መሠረት ከተቃወመ እና ለማቀናበር ከፍ ያሉ ሕጋዊ ምክንያቶች የሌሉ ከሆነ፤ ወይም

(መ) የግል ዳታ የተቀናበረው ሕጋዊ መሠረት ሳይኖረው ከሆነ

የግል ዳታው ያለ ምንም ክፍያና ያላግባብ መዘግየት እንዲደመሰስ የመጠየቅ መብት አለው።

(2) የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ይፋ ካደረገ፣ ዳታውን ለሚያቀናብሩ ሶስተኛ ወገኖች፣ የዳታው ባለቤት ከዳታው ጋር የተያያዙ ሊንኮችንና፣ ቅጂዎችን እንዲደመሰሱ የጠየቀ መሆኑን ለመግለጽ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

(3) የግል ዳታን ማቀናበር

(ሀ) በማሕበራዊ ጤና መስክ ለሕዝብ ጥቅም ተብለው ለተለዩ ምክንያቶች፣

(ለ) የዳታ ባለቤቱ መብቶችና መሠረታዊ ነጻነቶችን የሚጥስ የታወቀ ሥጋት ከሌለ፤ ለታሪካዊ፣ ለስታስቲካዊ ወይም ለሳይንስ ምርምር ዓላማ፣

(ሐ) የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ለማቀናበር ያለበትን ሕጋዊ ግዴታ ለመወጣት፣ ወይም ለሕዝብ ጥቅም በሚል የሚከናወነውን ተግባር ለመፈጸም፣ ወይም ዳታ ተቆጣጣሪው ከያዘው ሥልጣን በመነጨ ኃላፊነቱን ለመወጣት ወይም ሥልጣኑን ለመተግበር፣ ወይም

(መ) ሕጋዊ መብትን ለማቋቋም፣ ለመተግበር ወይም ለመከላከል

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተፈጻሚ አይሆኑም።

**40. ማቀናበርን መገደብ**

(1) የዳታ ባለቤቱ

(ሀ) የዳታ ባለቤቱ በዳታው ትክክለኛነት ላይ ተቃውሞ ያቀረበና የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተሰጠው፣

(ለ) የዳታ ተቆጣጣሪው ለማቀናበር የማይፈልገው፣ ነገር ግን የዳታው ባለቤት ሕጋዊ መብቱን ለማቋቋም፣ ለመተግበር ወይም ለመከላከል የሚፈልገው የግል ዳታ፣

(ሐ) የዳታ ማቀናበሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለው፣ እና የዳታው ባለቤት የግል ዳታው እንዳይደመሰስ ተቃውሞ ያቀረበና በምትኩ ማቀናበሩ እንዲገደብ የሚል ጥያቄ ያቀረበ፣ ወይም

(መ) የዳታ ባለቤቱ በአንቀጽ 41 መሠረት ማቀናበሩ እንዲቆም ተቃውሞ አቅርቦ ከሆነና ዳታ ተቆጣጣሪው ያለው ሕጋዊ ምክንያቶች የዳታ ባለቤቱ ካለው መብት የሚበልጥ፣

ከሆነ የግል ዳታ ማቀናበር እንዲገደብ የመጠየቅ መብት አለው።

(2) የግል ዳታን ማቀናበር በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተገደበ ከሆነ

(ሀ) የግል ዳታን ከማከማቸት በስተቀር ዳታ የሚቀናበረው በዳታ ባለቤቱ ፈቃድ፣ ወይም ሕጋዊ መብትን ለማቋቋም፣ ለመተግበር ወይም ለመከላከል፣ ወይም የሌላን ሰው መብት ለመጠበቅ፣ ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ነው፤ እንደዚሁም

(ለ) የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ለማቀናበር የተቀመጠን ገደብ ከማንሳቱ በፊት ይህንኑ ለዳታው ባለቤት ማሳወቅ አለበት።

**41. የመቃወም መብት**

(1) የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታ ባለቤቱን ፍላጎቶች፣ መብቶች እና ነፃነቶች ወይም ሕጋዊ መብቱን ለማቋቋም፣ ለመተግበር ወይም ለመከላከል የሚያስችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች ካላቀረበ በስተቀር፤ የዳታ ባለቤቱ የግል ዳታው እንዳይቀናበር በጽሑፍ የመቃወም መብት አለው።

(2) የግል ዳታ የሚቀናበረው የቀጥታ ማርኬቲንግ ለማካሄድ የሚል ዓላማን ለማሳካት ከሆነ፣ የዳታ ባለቤቱ ፕሮፋይሊንግን ጨምሮ ከዚሁ የቀጥታ ማርኬቲንግ ጋር የተያያዙና እሱን የተመለከተ የግል ዳታ ማቀናበርን መቃወም ይችላል።

(3) የዳታ ባለቤቱ ከቀጥታ ማርኬቲንግ ጋር በተያያዘ የግል ዳታው እንዳይቀናበር ከተቃወመ፣ የግል ዳታው ይህንን ዓላማ አስመልክቶ ማቀናበር አይቻልም።

(4) በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገጉት መብቶች የዳታው ባለቤት በግልጽ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

**42. አውቶሜትድ በሆኑ መሣሪያዎች በግለሰብ ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች**

(1) ማንኛውም የዳታ ባለቤት የሕግ ውጤት የሚያስከትል ወይም አሉታዊ ጫና የሚያሳድርበትንና ፕሮፋይሊንግን ጨምሮ አውቶሜትድ በሆኑ መሳሪያዎች ብቻ የሚሰጡ ውሳኔዎችን የመቃወም መብት አለው።

(2) ውሳኔው

(ሀ) በዳታ ባለቤቱ እና በዳታ ተቆጣጣሪው መካከል ውል ለመግባት፣ ወይም ውል ለመፈጸም አስፈላጊ ስለሆነ፣

(ለ) ዳታ ተቆጣጣሪው በሚገዛበትና የዳታ ባለቤቱን መብቶች፣ ነፃነቶች እና ሕጋዊ ጥቅሞች ለመጠበቅ ተስማሚ እርምጃዎችን በደነገገ ሕግ፣ ወይም

(ሐ) በዳታ ባለቤቱ ግልጽ ፈቃድ መሠረት

የተሰጠ ከሆነ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ አይሆንም።

(3) ከግለሰብ ጋር የተዛመዱ የተወሰኑ ግላዊ ጉዳዮችን ለመገምገም የታሰበ በአውቶሜትድ መሳሪያዎች የሚደረግ የግል ዳታ ማቀናበር፣ ጥንቃቄ በሚፈልግ የግል ዳታ ላይ ማካሄድ አይቻልም።

(4) በንዑስ አንቀጽ (2) ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች፣ ዳታ ተቆጣጣሪው በአንቀጽ 35 መሠረት ለዳታ ባለቤቱ ከሚሰጠው ኢንፎርሜሽን ውስጥ፤ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተጠቀሰው ዓይነት ውሳኔ ለማሳረፍ የተደረገ ማቀናበር መኖሩን እና እንደዚህ ዓይነቱ ማቀናበር በዳታ ባለቤቱ ላይ የሚያስከትለውን ውጤቶች ማካተት አለበት።

(5) በንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) ወይም (ሐ) በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታ ባለቤቱን መብቶች፣ ነፃነቶች እና ሕጋዊ ፍላጎቶች ለመጠበቅ ተስማሚ የሆኑ እርምጃዎችን መተግበር አለበት። በተለይም የዳታ ባለቤቱ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ መደረግ አለበት።

## 43. <u>የዳታ ፖርታቢሊቲ መብት</u>

(1) የዳታ ባለቤቱ እሱን አስመልክቶ ለዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ለዳታ አቀናባሪው የሰጠውን ዳታ፤ በተዋቀረ፣ በተለምዶ ጥቅም ላይ በሚውል እና በማሽን ሊነበብ በሚችል ቅርጽ የማግኘት መብት አለው።

(2) የዳታ ባለቤቱ በንዑስ አንቀጽ (1) ያገኘውን ዳታ ወደ ሌላ ዳታ ተቆጣጣሪ ወይም ዳታ አቀናባሪ ያለምንም ዕንቅፋት የማስተላለፍ መብት አለው።

(3) በቴክኒካዊ ሁኔታ የሚቻል ከሆነ፣ የዳታ ባለቤቱ የግል ዳታው ከአንድ የዳታ ተቆጣጣሪ ወይም አቀናባሪ ወደ ሌላ በቀጥታ እንዲተላለፍለት የማድረግ መብት አለው።

(4) በዚህ አንቀጽ ሥር ያለው መብት

(ሀ) ማቀናበሩ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ለሚከናወን ተግባር ወይም ኃላፊነትን ለመወጣት የተደረገ ከሆነ፣ ወይም

(ለ) የሌሎች ሰዎች መብቶች እና ነጻነቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ

ተፈፃሚ አይሆንም።

(5) የዳታ ተቆጣጣሪ ወይም የዳታ አቀናባሪ የዳታ ፖርታቢሊቲ ጥያቄዎችን ያለ ምንም ክፍያ እና ያላግባብ መዘግየት መፈጸም አለበት።

## 44 <u>መብትን ማስከበር</u>

(1) የዳታ ባለቤቱ ሕጋዊ ወራሽ የዳታ ባለቤቱ ከሞተ በኋላ በማንኛውም ጊዜ የዳታ ባለቤቱ የነበሩትን መብቶች ማስከበር ይችላል።

(2) የዳታ ባለቤቱ ሕጻን ልጅ ከሆነ፣ ወላጅ ወይም ሞግዚቱ የዚህን ልጅ መብት ማስከበር ይችላል።

(3) የዳታ ባለቤቱ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን መብቶችን እንዳይጠቀም የተከለከለ ወይም መብቱን ለመጠቀም የማይችል ከሆነ፣ ሞግዚት ወይም አሳዳሪው ሆኖ በፍርድ ቤት የተሾመ ሰው የዳታ ባለቤቱን መብቶች ማስከበር አለበት።

(4) በንዑስ አንቀጽ (1) - (3) ከተዘረዘሩት ውጭ በሆኑ ጉዳዮች፣ የዳታው ባለቤት በጽሑፍ የሾመው ማንኛውም ሰው እነዚህን መብቶች ሊያስከብር ይችላል።

https://chilot.me



## ምዕራፍ አምስት
## ዳታ ተቆጣጣሪዎች እና ዳታ አቀናባሪዎች

## ክፍል አንድ
## የዳታ ተቆጣጣሪዎች ምዝገባ

**45. ያለምዝገባ ዳታ ማቀናበር ስለመከልከል**

(1) ዳታ ተቆጣጣሪ ወይም ዳታ አቀናባሪ በኮሚሽኑ የምዝገባ ሥርዓት ውስጥ ያልተካተተ ከሆነ፣ የግል ዳታ አያቀናብሩም።

(2) ያለምዝገባ ግላዊ ዳታን ማቀናበር ወንጀል ነው፤ ይህን ሲፈጽም የተገኘ የዳታ ተቆጣጣሪ ይቀጣል።

(3) ማንኛውም ዳታ ተቆጣጣሪም ሆነ ዳታ አቀናባሪ ለመመዝገብ ሲፈልግ፣ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማመልከቻውን ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤ ማመልከቻው ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ቅጽ መቅረብ አለበት።

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ በፅሁፍ መደረግ አለበት፤ ማመልከቻው

(ሀ) የአመልካቹን የንግድ ስም እና ሙሉ አድራሻን፣

(ለ) ድርጅቱ የውጭ ድርጅት ከሆነ የተወካዩን ስምና አድራሻን፣

(ሐ) የግል ዳታው መግለጫ እና የግል ዳታቸው የሚቀናብርላቸው ሰዎች ምድብን፣

(መ) አመልካቹ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ስለመያዙ ወይም ሊይዝ እንደሚችል የሚያሳይ መግለጫን፣

(ሠ) የግል ዳታ የሚቀናበርበት ወይም ሊቀናበር የሚችልበት ምክንያት የሚገልጽ መግለጫን፣

(ረ) አመልካቹ የግል ዳታን ተደራሽ ሊያደርግለት የሚፈልገውን ተቀባይ መግለጫን፣

(ሰ) አመልካቹ የግል ዳታን ሊያስተላልፍ የሚፈልጋቸው የሶስተኛ ወገኖች የሥልጣን ክልል ስም ወይም መግለጫን፣

(ሸ) በአመልካቹ የተያዘ የግል ዳታ ባለቤት የሆኑ ሰዎች ምድብ ወይም ከተቻለ የግለሰቦቹ ስም ዝርዝርን፣

(ቀ) ዳታውን ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች ጠቅላላ መግለጫን፣ እና

(በ) ሌላ ማንኛውም ዓይነት ኮሚሽኑ የሚጠይቀው ኢንፎርሜሽንን

ማካተት አለበት።

(5) አመልካቹ በመመሪያው መሠረት የሚጠየቁ ክፍያዎችን መፈፀም አለበት።

(6) ማንኛውም የዳታ ተቆጣጣሪም ሆነ የዳታ አቀናባሪ በንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት ሆነ ብሎ የሃሰት ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠና፣ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ከ100 ሺህ ብር ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣት እና ከ5 ዓመታት ባልበለጠ እስራት ይቀጣል።

(7) ዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ለሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ዓላማዎች ማቀናበር ከፈለገ፣ ኮሚሽኑ እያንዳንዱን ዓላማ በመዝገብ ውስጥ ለብቻው ማካተት አለበት።

**46. ምዝገባን የመከልከል ሥልጣን**

(1) በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ከቀረበ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ በመዝገብ እንዲካተት የቀረበው ዝርዝር ኢንፎርሜሽን በቂ ካልሆነ ኮሚሽኑ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል።

(2) ኮሚሽኑ የዳታ ተቆጣጣሪውን የምዝገባ ጥያቄ ካልተቀበለ፣ በአሥራ አራት ቀናት ውስጥ
(ሀ) ውሳኔውንና ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት፣ እንደዚሁም
(ለ) በውሳኔው ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችል በመግለጽ
በፅሁፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።
(3) የምዝገባ ማመልከቻን ውድቅ ማድረግ በድጋሚ ማመልከትን አይከለክልም።

## 47. የምዝገባ ውጤቶች

(1) ኮሚሽኑ ማመልከቻው ለምዝገባ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው በመዝገብ ይጽፈዋል።
(2) እያንዳንዱ በመዝገብ የተጻፈ ማመልከቻ
(ሀ) በአንቀፅ 45(4) መሠረት የሚመዘገቡ፣ ወይም እንደ ሁኔታው ሌሎች በአንቀፅ 48 መሠረት የተደረጉ የማሻሻያ ኢንፎርሜሽንን፣ እንደዚሁም
(ለ) ኮሚሽኑ በመመሪያ መሠረት እንዲካተት የሚጠይቃቸው ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን
ማካተት አለበት ።
(3) ኮሚሽኑ አመልካቹ የተቀመጠውን ክፍያ ሲፈጽም የምዝገባ ሰርተፊኬት ይሰጠዋል።
(4) በንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የሚሰጠው የምዝገባ ሰርተፊኬት ለሁለት ዓመታት ያገለግላል፤ ቅድመ ሁኔታውም ሲሟላ በየሁለት ዓመቱ ይታደሳል።

## 48. ማሻሻያን የማሳወቅ ግዴታ

(1) የዳታ ተቆጣጣሪዎች በአንቀፅ 45(4) መሠረት መመዝገብ ያለበትን ኢንፎርሜሽን የተመለከቱ ማሻሻያዎች ለኮሚሽኑ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።
(2) በንዑስ አንቀፅ (1) የተቀመጠውን ድንጋጌ የጣሰ ማንኛውም ተቆጣጣሪ ወይም የዳታ አቀናባሪ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከ50 ሺህ ብር ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
(3) በንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት በሚወጣው መመሪያ መሠረት ኮሚሽኑ የማሻሻያ ማሳወቂያውን እንደተቀበለ፣ ኮሚሽኑ ማሳወቂያውን መነሻ በማድረግ አግባብነት ያለውን ማሻሻያ በመዝገቡ ላይ ያሰፍራል።

## 49. ከመዝገብ መፋቅ

ኮሚሽኑ ጥያቄው በመዝገቡ ላይ ባለ ሰው በማንኛውም ጊዜ ሲቀርብለት ይህንን ስም ከመዝገቡ ላይ ይፍቃል።

## 50. ምዝገባን ስለመሠረዝ

ኮሚሽኑ በቂ ምክንያት ካለው ምዝገባውን የመሠረዝ ሥልጣን አለው።

## 51. ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ

(1) ኮሚሽኑ በመዝገብ የተካተተ ኢንፎርሜሽን
(ሀ) ኅብረተሰቡ አመቺ በሆነ ሰዓትና ያለምንም ክፍያ መመርመር የሚያስችለውን ፋሲሊቲ ማቅረብ፣ እና
(ለ) ሌሎች ተገቢ ሆነው ያገኛቸውን ፋሲሊቲዎች ማመቻቸት
አለበት።

(2) ኮሚሽኑ የክፍያ መመሪያ በሚደነግገው መሠረት ክፍያ ሲፈጸም፣ በመዝገቡ ውስጥ የተካተተ ዝርዝር ኢንፎርሜሽንን በተመለከተ ለማንኛውም ሰው የተረጋገጠ የፅሁፍ ቅጅ ይሰጣል።

**52. <u>የዳታ ጥበቃ አፊሰር መሾም</u>**

(1) የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው

(ሀ) በፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር ከሚወድቁ ጉዳዮች በስተቀር፣ የመንግስት አካል ከሆነ፣

(ለ) ዋነኛ ተግባር በባህርያቸው፣ በወሰናቸው ወይም በዓላማቸው በዳታ ባለቤቶች ላይ መጠነ ሰፊ የሆነና በመደበኛነት በተደራጀ አግባብ የሚደረግ የማቀናበር ሥራ ከሆነ፣ ወይም

(ሐ) ዋነኛ ተግባር መጠነ ሰፊ የሆነ ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ማቀናበር ከሆነ

ራሱ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ የዳታ ጥበቃ አፊሰር መምረጥ ወይም መሾም አለበት።

(2) የዳታ ጥበቃ አፊሰሩ የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው ሠራተኛ ሊሆንና፤ የጥቅም ግጭት እስከሌለ ድረስ፤ በተደራቢነት ሌሎች ሥራዎችና ግዴታዎችን የሚፈፅም ሊሆን ይችላል።

(3) የዳታ ጥበቃ አፊሰሩ ለእያንዳንዱ ድርጅት በቀላሉ ተደራሽ እስከሆነ ድረስ ተቋሞች በጋራ አንድ የዳታ ጥበቃ አፊሰር ሊሾሙ ይችላሉ።

(4) የዳታ ተቆጣጣሪዎቹ ወይም የዳታ አቀናባሪዎቹ የመንግሥት አካላት ከሆኑ፣ ተቋማዊ አወቃቀራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንድ የዳታ ጥበቃ አፊሰር ለተለያዩ የመንግሥት አካላት በጋራ ሊሰየም ይችላል።

(5) አንድ ግለሰብ አስፈላጊ የሆነ የትምህርት እና የሞያ ዝግጅት ማለትም ከዳታ ጥበቃ ጋር ተያያዥ የሆነ ዕውቀት እና የቴክኒክ ልምድ ካለው የዳታ ጥበቃ አፊሰር ሆኖ ሊመረጥ ወይም ሊሾም ይችላል።

(6) የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ዳታ አቀናባሪው የዳታ ጥበቃ አፊሰሩን ሙሉ አድራሻ በህትመት ለሶስተኛ ወገኖች እና ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት።

(7) የሚከተሉት ማለትም

(ሀ) በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች በተደነገጉት የዳታ ማቀናበር መስፈርቶች ዙሪያ የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው እና ሠራተኞቻቸው ሥራቸውን በአግባቡ እንዲፈጽሙ ማገዝ፣

(ለ) ዳታ ተቆጣጣሪውን ወይም ዳታ አቀናባሪውን በመወከል ይህ አዋጅ መከበሩን ማረጋገጥ፣

(ሐ) በዳታ ማቀናበር ሥራዎች ውስጥ የሚሳተፉ ሠራተኞች አቅም እንዲጎለበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

(መ) የዳታ ጥበቃ ባመጣው ተጽዕኖ ዙሪያ የሚደረጉ ግምገማዎች ላይ አስተያየት ማቅረብ፣

(ሠ) ከኮሚሽኑና ከሌሎች በዳታ ጥበቃ ዙሪያ ከሚሰሩ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቶች ጋር መተባባር

የዳታ ጥበቃ አፊሰሩ ኃላፊነቶች ናቸው።

## ክፍል ሁለት
## የዳታ ተቆጣጣሪዎች ግዴታዎች

**53. <u>የቴክኒክና ተቋማዊ እርምጃዎች</u>**

(1) ዳታ ተቆጣጣሪው ዳታ ማቀናበሩ በዚህ አዋጅ መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ ቴክኒካዊና ተቋማዊ እርምጃዎችን መተግበር አለበት።

(2) በንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሱ እርምጃዎች

(ሀ) ተገቢውን የዳታ ደህንነት እና ተቋማዊ እርምጃዎች ማስፈፀምን፣

(ለ) የማቀናበር ሥራዎችን በጠቅላላ ሪከርድ አድርጎ ማስቀመጥን፣
(ሐ) የዳታ ጥበቃ ያመጣው ተጽዕኖን የመገምገም ሥራ መሥራትን፣
(መ) ኮሚሽኑንን ፈቃድ መጠየቅ ወይም ማማከር በሚገባ ጊዜ ይሄንኑ መፈጸምን፣ እና
(ሠ) የዳታ ጥበቃ ኦፊሰር መመደብን
ያካትታሉ።

(3) ማንኛውም የዳታ ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀፅ ድንጋጌ ውስጥ የተጠቀሱት እርምጃዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ሥራ ላይ ማዋል አለበት።

**54. <u>የግል ዳታ ጥሰትን ማሳወቅ</u>**

(1) የግል ዳታ ጥሰት በሚኖርበት ጊዜ፣ የግል ዳታ ጥሰቱ የግለሰብ መብቶችና ነፃነቶች አደጋ ላይ የማይጥል ካልሆነ በስተቀር፤ ዳታ ተቆጣጣሪው ያላስፈላጊ መዘግየት እና የሚቻል ከሆነ ጥሰቱን ካወቀበት ከ72 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የግል ዳታ ጥሰቱን ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት።

(2) የግል ዳታ ጥሰቱ ለኮሚሽኑ በ72 ሰዓታት ውስጥ ካልተገለጸ፣ ማሳወቂያው የዘገየበትን ምክንያት አካቶ መቅረብ አለበት ።

(3) ዳታ አቀናባሪው የግላዊ ዳታ ጥሰት መኖሩን እንዳወቀ ያለምንም መዘግየት ለዳታ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ አለበት።

(4) በንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርበው የግል ዳታ ጥሰት ማሳወቂያ
(ሀ) የግል ዳታ ጥሰቱን ባህርይ እና ከተቻለ የዳታ ባለቤቶቹን ምድቦችና ግምታዊ ቁጥር፣ እንደዚሁም የግል ዳታ ምድቦችና ግምታዊ ቁጥር፣
(ለ) የዳታ ጥበቃ ኦፊሰሩን ሙሉ አድራሻ ወይም ሌላ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚቻልበትን አግባብ፣
(ሐ) የግል ዳታ ጥሰቱ ሊያስከትል የሚችለው ውጤቶች፣ እና
(መ) ለግል ዳታ ጥሰቱ ምላሽ ለመስጠት በዳታ ተቆጣጣሪው የተወሰዱ ወይም ሊወሰዱ የታሰቡ እርምጃዎች፣ እንደዚሁም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ አሉታዊ ውጤቶችን ለመቀነስ የሚወሰዱ ዕርምጃዎችን
መግለጽ አለበት።

(5) ኢንፎርሜሽኑን በአንድ ጊዜ ማቅረብ በማይቻልበት ጊዜ፣ ኢንፎርሜሽኑ እንደተገኘ ያለምንም ተጨማሪ መዘግየት ማቅረብ ይቻላል።

(6) ኮሚሽኑ የዳታ ተቆጣጣሪው በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት መሥራቱን ለመገምገም እንዲያግዘው፣ ዳታ ተቆጣጣሪው ከግል ዳታ ጥሰቱ ጋር የተያያዙ ዕውነታዎችንና ውጤታቸውን፣ እንደዚሁም የተወሰዱ የዕርምት ዕርምጃዎችን በሰነድ ማስቀመጥ አለበት።

**55. <u>የግል ዳታ ጥሰትን ለዳታ ባለቤቱ ኮሙኒኬት ማድረግ</u>**

(1) የግል ዳታ ጥሰቱ የዳታ ባለቤቱን መብትና ነጻነት አደጋ ውስጥ የሚከት ሆኖ ሲገኝ፣ ዳታ ተቆጣጣሪው ያለምንም መዘግየትና ከተቻለ ጥሰቱን ባወቀ 72 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለዳታ ባለቤቱ መግለጽ አለበት።

(2) ለዳታ ባለቤቱ የሚቀርበው መግለጫ የግል ዳታ ጥሰቱን ባህርይ በግልጽ ቋንቋ የሚያብራራና በአንቀጽ 54(4) (ለ) – (መ) የተዘረዘረውን ኢንፎርሜሽን ያካተተ መሆን አለበት።

(3) ዳታ ተቆጣጣሪው

(ሀ) ተገቢውን የቴክኒክና ተቋማዊ የመከላከል እርምጃዎችን ከወሰደ፣ እና እነዚህ እርምጃዎች በጥሰቱ በተጎዱ የግል ዳታዎች ላይ ከተተገበሩ፣ በተለይም ዳታ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሊረዳው እንዳይችል ለማድረግ እንደ መመስጠሪያ የመሰሉ እርምጃዎች የተወሰዱ ከሆነ፣

(ለ) በንዑስ አንቀጽ(1) ላይ የተገለጸው የዳታ ባለቤትን መብቶችና ነፃነቶች አደጋ ላይ የሚጥሉ ሁኔታዎች ከዚህ በኋላ ሊከሰቱ እንዳይችሉ ለማድረግ ተከታታይ እርምጃዎች ከወሰደ፣ ወይም

(ሐ) የዳታ ባለቤቱን ኮሙኒኬት ማድረግ ተመጣጣኝ ያልሆነ ጥረት ውስጥ የሚከተው ከሆነና፤ ዳታ ተቆጣጣሪው የአህዝቦት ሥራዎች በመሥራቱ ወይም ተመሳሳይ እርምጃዎችን በመውሰዱ የዳታ ባለቤቱ ጥሰቱን በተመለከተ ኢንፎርሜሽን ያገኘ ከሆነ

የግል ዳታ ጥሰቱን ለዳታ ባለቤቱ መግለጽ አያስፈልግም።

(4) የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታ ጥሰቱን ለዳታ ባለቤቱ ካላሳወቀ፣ ኮሚሽኑ የግል ዳታ ጥሰቱ ሊያደርስ የሚችለውን የሥጋት ደረጃ ከመረመረ በኋላ የዳታ ጥሰቱን ለዳታ ባለቤቱ እንዲያሳውቅ ሊያዘው ይችላል።

## 56. <u>የቅድመ ደህንነት ማጣራት</u>

(1) ኮሚሽኑ በዳታ ተቆጣጣሪው ወይም በዳታ አቀናባሪው የሚደረግ የዳታ ማቀናበር ወይም ማስተላለፍ ሥራ የዳታ ባለቤቱን ግላዊ መብት አደጋ ውስጥ የሚከት ሆኖ ሲያገኘው፣ በአንቀፅ 27(4)፣ (5) እና (6) ላይ የተዘረዘሩ የደህንነት ዕርምጃዎችን ዳታ ከማቀናበሩ ወይም ከመተላለፉ በፊት ኮሚሽኑ ሊመረምር እና ሊገመግም ይችላል።

(2) ኮሚሽኑ በአንቀፅ 27(4)፣ (5) እና (6) መሠረት በዳታ ተቆጣጣሪ ወይም በዳታ አቀናባሪ ላይ የተጣሉ የደህንነት ዕርምጃዎችን በተመለከተ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ተገኝቶ ተጨማሪ ምርመራ እና ግምገማ ማካሄድ ይችላል።

## 57. <u>የማቀናበር ሥራዎችን ሪከርድ ማድረግ</u>

(1) ማንኛውም ዳታ ተቆጣጣሪም ሆነ ዳታ አቀናባሪ በኃላፊነቱ ሥር ያሉትን የማቀናበር ሥራዎች ጠቅላላ በተመለከተ ሪከርድ መያዝ አለበት።

(2) ሪከርዱ

(ሀ) የዳታ ተቆጣጣሪውን ወይም የዳታ አቀናባሪውን ስምና አድራሻ፣ እንደዚሁም እንዳግባብነቱ የተወካዩንና የዳታ ጥበቃ ኦፊሰሩን ስምና አድራሻን፣

(ለ) የማቀናበሩን ዓላማን፣

(ሐ) የዳታ ባለቤቶችና የግል ዳታ ምድቦችን መግለጫን፣

(መ) በውጭ አገር ያሉ ተቀባዮችን ጨምሮ የግል ዳታውን ሲቀበሉ የነበሩ ወይም የሚላክላቸው ተቀባዮች ምድቦች መግለጫን፣

(ሠ) ማንኛውም ወደ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል የተላለፈ ዳታ፣ እና የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን፣

(ረ) ከተቻለ የተለያዩ የዳታ ምድቦች የሚደመሰሱበት የጊዜ ገደብን፣ እንደዚሁም

(ሰ) የዳታ ደህንነት ማረጋገጫ ዘዴዎች መግለጫን

ማካተት አለበት ።

(3) የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው ሲጠየቅ ሪከርዱን ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት።

## 58. <u>የዳታ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማ</u>

(1) የዳታ ማቀናበር ሥራ በባህርዩ፣ በወሰኑ፣ በአውዱ እና በዓላማው የዳታ ባለቤቱ መብቶችና ነፃነቶች ላይ ከፍተኛ ስጋት የሚደቅን ከሆነ፣ ማንኛውም የዳታ ተቆጣጣሪ ወይም የዳታ አቀናባሪ ዳታን ከማቀናበሩ በፊት የማቀናበር ሂደቱ በግል ዳታ ጥበቃ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖ መገምገም አለበት።

(2) በንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው የማቀናበር ሂደት

(ሀ) ፕሮፋይሊንግን ጨምሮ በአውቶሜትድ መሳሪያዎች የተመሠረተ፣ የተደራጀና ሰፊ የሆነ ከግለሰቦች ግላዊ ሕይወት ጋር የተያያዘ፣ እንደዚሁም በግለሰቦች ላይ ለሚሰጥና ሕጋዊ ውጤት ለሚያመጣ ውሳኔ መነሻ የሆነ ወይም በግለሰቦች ላይ ጉልህ ጫና የሚያሳድር፣

(ለ) መጠነ ሰፊና ጥንቃቄ የሚፈልግ የግል ዳታ ላይ የሚካሄድ፣

(ሐ) መጠነ ሰፊና ሕዝብ የሚሰበሰብበትን ቦታ በተደራጀ መንገድ መቆጣጠርን የተመለከተ፣ እንደዚሁም

(መ) ሌላ ከኮሚሽኑ ጋር ምክክር ማድረግ የሚጠይቅ ማናቸውም ዓይነት

ማቀናበርን ያካትታል።

(3) ግምገማው

(ሀ) ሊተገበር የተፈለገው የማቀናበር ሥራን በተደራጀ አግባብ ማብራራት፣ እንዳግባቡ የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው ሊያሳካ የሚፈልገው ሕጋዊ ፍላጎትን ጨምሮ የማቀናበሩን ዓላማ፣

(ለ) የማቀናበሩ ሥራ ከዓላማው ጋር ሲነጻጸር የአስፈላጊነቱንና የተመጣጣኝነቱን ግምገማ፣

(ሐ) የዳታ ባለቤቱ መብቶችን እና ነፃነቶች ላይ የሚጥለው የሥጋት ደረጃ ግምገማ፣ እንደዚሁም

(መ) የዳታ ባለቤቱን እና ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎች መብቶች እና ሕጋዊ ጥቅሞች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ስጋቱን ለመግታት የሚወሰዱ ዕርምጃዎች፣ እንደዚሁም የሚወሰዱ የደህንነት ዕርምጃዎች እና የግል ዳታ ጥበቃን ለማረጋገጥና ከዚህ አዋጅ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማሳየት የሚወሰዱ የጥንቃቄ፣ የደህንነት እርምጃዎችንና የተደረጉ ዘዴዎች፣ በዚህ አዋጅ መሠረት መደረጉን

የሚገልጽ መግለጫ ሊያካትት ይገባል።

(4) ተገቢ ሆኖ ሲገኝና የንግድ ወይም የመንግሥት ፍላጎቶችን ወይም የማቀናበር ሥራውን ደህንነት በማይጣረስ መልኩ፤ የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው ስለታሰበው ማቀናበር  የዳታ ባለቤቱን ዕይታ ሊጠይቅ ይችላል።

**59. <u>ኮሚሽኑን ፈቃድ መጠየቅና ማማከር</u>**

(1) ማንኛውም የዳታ ተቆጣጣሪ ወይም የዳታ አቀናባሪ የታሰበው የማቀናበር ሥራ ከአዋጁ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥና በተለየም ዳታ ተቆጣጣሪውም ሆነ ዳታ አቀናባሪው የግል ዳታን ወደ ሶስተኛ ወገን የሥልጣን ክልል ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ተገቢውን የጥበቃ እርምጃዎች መውሰድ በማይቻልበት ጊዜ፣ በዳታ ባለቤቱ ላይ የሚያደርሰውን ሥጋት ለመቀነስ ከኮሚሽኑ ቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

(2) የዳታ ተቆጣጣሪውም ሆነ የዳታ አቀናባሪው የግል ዳታን ከማቀናበሩ በፊት የታቀደው የማቀናበር ሥራ ከአዋጁ ጋር የማይጣረስ መሆኑን ለማረጋገጥና በዳታ ባለቤቶች ላይ የሚያስከትለውን የሥጋት ጫና ለመቀነስ

(ሀ) የዳታ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማው የማቀናበሩ ሥራ በባሕርዩ፣ በወሰኑ እና በዓላማው በከፍተኛ ደረጃ ለሥጋት የተጋለጠ መሆኑን የሚያመላክት፣ ወይም

(ለ) ኮሚሽኑ  የማቀናበሩ ሥራ በባሕርዩ፣ በወሰኑ እና በዓላማው የዳታ ባለቤቶችን መብቶችና ነጻነቶች በከፍተኛ ደረጃ ለሥጋት ያጋልጣል ብሎ ሲገምት

ኮሚሽኑን አስቀድሞ ማማከር አለበት።

(3) ኮሚሽኑ የታሰበው ማቀናበር ከአዋጁ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ካገኘው በተለየም ማቀናበሩ ሊያስከትላቸው የሚችላቸው ሥጋቶች በበቂ ሁኔታ ካልተለዩ እና ካልተቀነሱ፣ የታቀደውን ማቀናበር ይከለክላል፤ ከአዋጁ ጋር አለው የተባለውን አለመጣጣም በተመለከተ ሊወሰድ የሚገባውን ተገቢ ዕርምጃ ምን እንደሆነ ያሳውቃል።

(4) ኮሚሽኑ በንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሠረት ቅድመ ምክክር የሚያስፈልጋቸውን የማቀናበር ሥራዎች ዘርዝሮ ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት።

(5) ዳታ ተቆጣጣሪው ወይም ዳታ አቀናባሪው የዳታ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማው ሰነድንና፤ ሲጠየቅ ደግሞ ሌላ ማንኛውንም መረጃ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት።

## 60 በማሽኖሽ ዲዛይንና ሥሪት የሚደረግ የዳታ ጥበቃ

(1) የዳታ ተቆጣጣሪው፣ እንዳግባብነቱ የዳታ አቀናባሪው፣ በጋራ፤ የዳታ ማቀናበሪያው መንገድ ተለይቶ በሚወሰንበትና ማቀናበሩ በሚከናወንበት ጊዜ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ

(ሀ) የግል ዳታ ማቀናበር መርሕ ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸማቸውን፣ እንደዚሁም

(ለ) የዳታ ባለቤቶችን መብት የሚያስከብሩ የደህንነት እርምጃዎች የተካተቱ መሆናቸውን

ማረጋገጥ አለባቸው።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉት የደህንነት እርምጃዎች፣ ቴክኖሎጂ የደረሰበትን ደረጃ፣ ትግበራው የሚፈጀውን ወጪ፣ እንደዚሁም የማቀናበሩን ባህርይ፣ ወሰን፣ አግባብና ዓላማ፤ እንደዚሁም ማቀናበሩ በግለሰቦች መብቶችና ነጻነቶች ላይ ሊያመጣ የሚችለውን የአደጋ ሥጋት ጫና ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

(3) የዳታ ተቆጣጣሪው በሥሪት ለእያንዳንዱ የተለየ ዓላማ አስፈላጊ የሆኑ የግል መረጃዎች ብቻ መቀናበራቸውን የሚያረጋግጥ ተገቢ የሆነውን ቴክኒካዊ እና ተቋማዊ እርምጃዎችን በሥራ ላይ ያውላል።

(4) የንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ በሚሰበሰበውን የግል ዳታ መጠን፣ የግል ዳታ በሚቀናበርበት መጠን፣ የግል ዳታ በሚከማችበት የጊዜ ርዝማኔ፣ እና በግል ዳታ ተደራሽነትን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

(5) በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የቴክኒክ እና ተቋማዊ እርምጃዎች የግል ዳታ በሥሪት ካለግለሰቡ ጣልቃ ገብነት ቁጥራቸው በውል ላልታወቁ ግለሰቦች ተደራሽ የማይደረግ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

## 61 የግል ዳታን የመደምሰስ ግዴታ

(1) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 25 በተቃራኒ የተደነገገ ካልሆነና፣ የግል ዳታ ተጠብቆ መቆየት ያለበት ጊዜ ከተገባደደ፣ እያንዳንዱ የዳታ ተቆጣጣሪ

(ሀ) በተቻለ ፍጥነት የግል ዳታን መደምሰስ ወይም መሰረዝ፣ ወይም

(ለ) ሪከርዱ የማን እንደሆነ እንዳይታወቅ ማድረግ

አለበት።

(2) የግል ዳታ ሪከርድ የሚደመሰስበት ወይም የሚሰርዝበት አግባብ፣ ዳታው መልሶ የሚነበብ እንዳይሆን ማድረግን በማረጋገጥ መሆን አለበት።

(3) የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ለያዘው ማንኛውም የዳታ አቀናባሪ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ያለበትን ግዴታ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

(4) በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማስታወቂያ የተቀበለ ማንኛውም የዳታ አቀናባሪ በተቻለ መጠን በፍጥነት በዳታ ተቆጣጣሪው የተገለጸውን ዳታ መደምሰስ አለበት።

**62 የጊዜ ገደቦችን ማክበር**

የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ለማስተካከል፣ ለመደምሰስ ወይም ማቀናበሩን ለመገደብ፣ ወይም የግል ዳታ ክምችት አስፈላጊነትን በተመለከተ በየጊዜው ለመገምገም የተቀመጡ የጊዜ ገደቦችን ለማክበር የሚያስፈልጉ አሠራሮችን መዘርጋት አለበት።

## ምዕራፍ ሰባት
## በአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ላይ የተጣሉ ገደቦች

**63 አጠቃላይ ገደቦች**

(1) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ላይ የሚጣል ገደብ ተፈጻሚ የሚሆነው፣ ገደብ መጣሉ በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ

(ሀ) በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለብሔራዊ ደህንነት፣ ለአገር መከላከያ እና ለሕዝብ ሠላም፣

(ለ) የቅጣት ውሳኔ አፈጻጸምን ጨምሮ ወንጀል ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለማነፍነፍ ወይም ክስ ለመመስረት፣

(ሐ) የመንግሥት የኤኮኖሚና የፋይናንስ ጥቅሞችን ጨምሮ ለአጠቃላይ የሕዝብ ጥቅም ዓላማ፣

(መ) የዳኝነት ነጻነትና የፍርድ ሂደቶችን ለመጠበቅ፣ ወይም

(ሠ) የዳታ ባለቤቱን ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት ለመጠበቅ

አስፈላጊና ተመጣጣኝ እርምጃ ከሆነ ነው።

(2) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የግል ዳታን ለታሪካዊ፣ ለስታስቲክስ ወይም ለሳይንሳዊ ምርምሮች ዓላማ በማቀናበር ላይ ገደብ የሚጣልባቸው በአንቀጽ 27(4)፣ (5) እና (6) የተደነገጉት የደህንነትና ተቋማዊ እርምጃዎች የዳታ ባለቤቱን መብቶችና ነጻነቶች ለመጠበቅ የሚተገበሩ ከሆነ ነው።

(3) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ከተጣሱ፣ የዳታ ባለቤቱ ወይም ኮሚሽኑ የግለሰቦች መብት እንዲከበር በፍርድ ቤት ክስ መመስረት ይችላሉ።

(4) የዚህ አዋጅ ማናቸውም ድንጋጌዎች በግል ዳታ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ገደብ የሚጣልባቸው፣ ድንጋጌዎቹ በግል ዳታ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆኑ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሳኔ ብሔራዊ ደህንነትን፣ የአገር መከላከያን እና የሕዝብ ሠላምን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነ ነው።

(5) ለብሔራዊ ደህንነት፣ ለአገር መከላከያ እና የሕዝብ ሠላምን ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው በማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተፈረመ ማረጋገጫ የዚህ ዕውነታ ማስረጃ ተደርጎ ይወሰዳል።

**64 ተጨማሪ ገደቦችን በመመሪያ የመደንገግ ሥልጣን**

ኮሚሽኑ ይፋ እንዳይደረግ በማናቸውም ሕግ የተከለከለ ወይም ገደብ የተጣለበት የግል ዳታ

(ሀ) የዳታ ባለቤቱ ጥቅሞችን፣ ወይም

(ለ) የሌሎች ግለሰቦችን መብቶችና ነጻነቶችን ለመጠበቅ አስፈላጊ ናቸው ብሎ ሲያምን፣

እነዚህን ገደቦች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ በመመሪያ በመደንገግ ገደቡን ማንሳት ይችላል።

## ምዕራፍ ስምንት

## አፈጻጸም

### 65 የአፈጻጸም ትዕዛዝ

(1) ኮሚሽኑ የዳታ ተቆጣጣሪው ወይም የዳታ አቀናባሪው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ጥሷል፣ በመጣስ ላይ ነው፣ ወይም ለመጣስ በዝግጅት ላይ ብሎ ከጠረጠረ፤ ኮሚሽኑ ለዚህ ሰው ቀነ ገደብ በማስቀመጥ ሊፈጽማቸው ይገባል ያላቸውን ተግባራት ዘርዝሮ በአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊያዘው ይችላል።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሟል በማለት ከጠረጠረ፣ ጉዳዩን በራሱ ሊመረምር ወይም ውክልና የተሰጠው ሌላ ተቋም ጉዳዩን እንዲመረምር ማድረግ ይችላል።

(3) በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ

(ሀ) የተጣሰውን፣ በመጣስ ላይ ያለውን ወይም ሊጣስ ያለውን የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ለይቶ ማሳወቅ፤

(ለ) ሊፈጸም ያለውን ጥሰት ሊያስተካክል ወይም ሊያስወግድ የሚችለውን እርምጃ ለይቶ ማሳወቅ፣

(ሐ) እነዚህ እርምጃዎች የሚተገበሩበት ከሃያ አንድ ቀናት ያላነሰ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ፣ እንደዚሁም

(መ) በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን መግለጽ

አለበት።

(4) የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝን ከፈጸመ ሃያ አንድ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ እንዳግባብነቱ ዳታ ተቆጣጣሪው ወይም አቀናባሪው

(ሀ) ለውጡን ጉዳዩ ለሚመለከተውን የዳታ ባለቤት፣ እንደዚሁም

(ለ) የትዕዛዙ መፈጸም የሚመለከተውን ዳታ በመሠረታዊ ደረጃ የሚቀይር ከሆነ፣ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ዕለት ጀምሮ ወደ ኃላ ባሉ አስራ ሁለት ወራቶች ጀምሮ ትዕዛዙ ከመፈጸሙ ዕለት በፊት እስካለው ዕለት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ዳታው ይፋ ለተደረገላቸው ሰዎች ለውጡን

ማሳወቅ አለበት።

(5) ኮሚሽኑ የዚህ አዋጅ መከበርን ለማረጋገጥ የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ አለመፈጸሙ የተሻለ ሆኖ ካገኘው፣ ትዕዛዙን ሊያነሳው ይችላል፤ ኮሚሽኑ ይህን ሲያደርግ አዲሱን ትዕዛዝ በጽሑፍ ማውጣትና ለሚመለከተው ሰው ማድረስ አለበት።

(6) ማንኛውም ሰው ያለምንም በቂ ምክንያት የአፈጻጸም ትዕዛዙን ለመፈጸም ካልቻለ፣ ወይም አላከብርም ካለ ጥፋት እንደፈጸመ ይቆጠራል፤ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥም ከ 50, 000 ብር በማይበልጥ መቀጮ እና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

### 66 መረጃ የማግኘት ሥልጣን

(1) ኮሚሽኑ የጽሑፍ ትዕዛዝ በማውጣትና የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ፣ ከማንኛውም ሰው

(ሀ) የግል ዳታ፣

(ለ) የግል ዳታ ማቀናበርን በተመለከተ ያለ ኢንፎርሜሽንና ዶክመንቴሽን፣

(ሐ) የግል ዳታ ከማቀናበር ጋር ተያያዥ የሆኑ የደኅንነት ኢንፎርሜሽን፣ እና

(መ) ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና የተሰጠውን ሥልጣን ለመፈጸም አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ተግባራት ለመፈጸም በትዕዛዙ ላይ ከተገለጹ ጉዳዮች ጋር ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ኢንፎርሜሽን

እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠየቀው ኢንፎርሜሽን ለኮሚሽኑ የሚሰጠው ወይም ተደራሽ የሚደረገው ሊወሰድ፣ ሊነበብ እና ደጋግሞ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችል መልኩ መሆን አለበት።

(3) ኢንፎርሜሽን ይፋ እንዳይሆን የሚከለክል ወይም የሚገድብ በሥራ ላይ ያለ የትኛውም ሕግ መኖሩ፣ ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ የተጠለበትን ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ኢንፎርሜሽን እንዳያቀርብ አይከለክልም።

(4) የንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ለብሔራዊ ደህንነት አስፈላጊ በሆኑ ኢንፎርሜሽኖች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

(5) በዚህ ድንጋጌ የሚሰጥ ትዕዛዝ በውስጡ፣ ትዕዛዙ የተሰጠው ሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ በትዕዛዙ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶችን የመቃወም መብት እንዳለው መግለጽ አለበት።

(6) በዚህ ድንጋጌ መሠረት መረጃን በተመለከተ ትዕዛዝ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ትዕዛዙን አለመፈጸም አይችልም። ትዕዛዝን አለመፈጸም ወንጀል ነው።

(7) ኮሚሽኑ የግል ዳታ ማቀናበር ሕጋዊ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል በቂ ኢንፎርሜሽን ማግኘት ካልቻለ፣ ኮሚሽኑ የዳታ ተቆጣጣሪው የግል ዳታን ከማከማቸት ውጪ በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዳያቀናበር መከልከል ይችላል።

## 67 <u>የአቤቱታዎች ምርመራ</u>

(1) የዳታ ባለቤቶች በዚህ አዋጅ ውስጥ የተቀመጡ መብቶቻቸው ሲጣሱ አቤቱታ የማቅረብ መብት አላቸው።

(2) ኮሚሽኑ በዳታ ባለቤት አቤቱታ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት የዚህ አዋጅ ወይም የሌሎች የበታች ሕጎች ድንጋጌዎች የተጣሱ፣ እየተጣሱ ወይም ሊጣሱ እንደሆነ ከጠረጠረ፣ ምርመራ በራሱ ሊያካሂድ ወይም ምርመራ እንዲደረግ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

(3) በንዑስ አንቀጽ (2) አግባብ መሠረት አቤቱታ ለኮሚሽኑ ሲቀርብ፣ ኮሚሽኑ

(ሀ) አቤቱታው በክፉ ልቦና የቀረበ ነው ካላለ በስተቀር፣ አቤቱታውን በራሱ መመርመር ወይም በሌላ ተቋም እንዲመረምር ማድረግ፣ እና

(ለ) የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በተቻለ ፍጥነት ለዳታ ባለቤቱ በጽሑፍ ሊያሳውቀውና የዳታ ባለቤቱ በውሳኔው ቅር የተሰኘ እንደሆነ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ መግለጽ

አለበት።

(4) በዚህ አዋጅ ውስጥ ያለ የትኛውም ድንጋጌ የዳታ ባለቤቱን እንዲወክል በጽሑፍ ውክልና ከተሰጠው ሰው ኮሚሽኑ አቤቱታ እንዳይቀበልና እንዳመረምር አይከለክልም፤ እንደዚሁም በዚህ አዋጅ የዳታ ባለቤቱን አስመልክተው የተደነገጉ ድንጋጌዎች በጠቅላላ በዳታ ባለቤቱ የተሾመ ወኪልንም ይጨምራሉ።

(5) ኮሚሽኑ ከዚህ ውጭ ካልፈቀደ በስተቀር በዚህ አዋጅ መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ አቤቱታ በጽሑፍ መቅረብ አለበት።

(6) አቤቱታ ማቅረብ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን በጽሑፍ ማቅረብ እንዲችል ኮሚሽኑ ተገቢ የሆነ ድጋፍ መስጠት አለበት ።

## 68 <u>ብርበራና መያዝ</u>

(1) በዚህ አዋጅ የተሰጠን ኃላፊነትን ለመወጣት አስፈላጊ ከሆነ፣ ኮሚሽኑ ወይም ውክልና የተሰጠው ሌላ ተቋም ወደ ቅጥር ግቢ መግባት፣ ፍተሻ ማካሄድ፣ እና መያዝ ይችላል።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሰው ዓላማ በፍርድ ቤት የተሰጠ የብርበራ ትዕዛዝ መቅረብ አለበት።

(3) ፍርድ ቤቱ በቃለ መሐላ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አግባብ የሆነውን ውሳኔ ይሰጣል።

(4) በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠ ትዕዛዝ የሚያገለግለው በትዕዛዙ ላይ ለተጠቀሰው የጊዜ ርዝማኔ ብቻ ነው፤ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙ ላይ አግባብ ነው ያላቸውን ሌሎች ሁኔታዎችን መጣል ይችላል።

(5) የብርበራ ትዕዛዝ የያዘ ኦፊሰር

(ሀ) ባለቤቱን ወይም በቅጥር ግቢው ውስጥ ያለውን ሰው ማንኛውንም ሰነድ፣ ሪከርድ ወይም ዳታ እንዲቀርብለት መጠየቅ፣

(ለ) እንዲህ ዓይነቱን ሰነድ፣ ሪከርድ ወይም ዳታ መመርመርና የእነዚህን ሙሉ ቅጂዎች ወይም ከፊል ክፍሎች መውሰድ፣ እንደዚሁም

(ሐ) የተቋሙን ባለቤት፣ ወይም በሥር ያሉ ተቀጣሪ ሠራተኞች፣ ወይም ሌሎች በቅጥር ግቢው ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን ጥያቄ ሲያቀርብላቸው በቃል ወይም በጽሑፍ አስፈላጊ የሆነ ትብብር እንዲሰጡት መጠየቅ

ይችላል።

(6) በኦፊሰሩ የተጠየቀው ኢንፎርሜሽን በማንኛውም የሜካኒካል ወይም የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ውስጥ የተከማቸ ወይም የተጠበቀ ከሆነ፣ ጥያቄው ኢንፎርሜሽኑ ተደራሽ እንዲሆን እንደዚሁም ሊታይና ሊነበብ በሚችል መልኩ ለመውሰድ የቀረበ ጥያቄ ተደርጎ ይወሰዳል።

## 69 <u>የኮሚሽኑን ሥራ ማደናቀፍ</u>

(1) ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተደነገገው ኃላፊነትን እንዳይወጣ የማድረግ ተግባር መፈጸም በወንጀል ያስጠይቃል፤ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥም ከ 50,000 ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት፣ ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

(2) የሚከተሉት ማለትም

(ሀ) ኮሚሽኑን በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን እንዳይፈጽም ማደናቀፍ፣

(ለ) ኮሚሽኑ የጠየቀውን ድጋፍ ወይም ኢንፎርሜሽን አለመስጠት፣

(ሐ) ኮሚሽኑ ወደ ሕንጻዎችና ቅጥር ግቢዎች እንዳይገባ መከልከል፣ ወይም ማንኛውም ሰው በቁጥጥር ሥር እንዳይውል መከላከል፣ ወይም

(መ) ለኮሚሽኑ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ ኢንፎርሜሽን መስጠት

በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ወንጀል ናቸው።

## 70 <u>በኮሚሽኑ የሚሰጥ የሥልጣን ውክልና</u>

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ማንኛውንም የምርመራ ወይም የአፈጻጸም ሥልጣን ለማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## 71 <u>ከግል ተጠያቂነት ነጻ መሆን</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት በኮሚሽኑ ሠራተኞች ወይም ውክልና በተሰጣቸው ተቋማት ሠራተኞች በቅን ልቦና የተፈጸመ ተግባር መነሻ በማድረግ የካሳ ጥያቄ ወይም ሌላ ክስ መመስረት አይቻልም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## በውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት

**72** **<u>የአመልካች የይግባኝ መብት</u>**

(1) ከግል ዳታው ጋር በተያያዘ የዳታ ተቆጣጣሪ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው የግል ዳታ ባለቤት በኮሚሽኑ ፊት ቀርቦ በውሳኔው ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል።

(2) የንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዳታ ባለቤቱ የግል ዳታ ከማቀናበር ጋር በተያያዘ ያሉትን ማናቸውም ቅሬታዎች በተመለከተ የኮሚሽኑን ትብብር የመጠየቅ መብት አለው።

**73** **<u>ይግባኝ የመጠየቂያ የጊዜ ገደብ</u>**

በአንቀጽ 72(1) መሠረት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ይግባኝ ይግባኝ የቀረበበት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ ቀን ውስጥ ለኮሚሽኑ በጽሑፍ መቅረብ አለበት።

**74** **<u>ይግባኝ ውድቅ ማድረግ</u>**

ኮሚሽኑ ከይግባኝ አቤቱታው በመነሳት አቤቱታ የቀረበበት የግል ዳታ ስለመኖሩ በቂ የሆነ ምክንያት አለ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል መነሻ ከሌለው፣ ወይም ይግባኙ በበቂ ምክንያት የተደገፈ አይደለም ብሎ ከደመደመ ይግባኙን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

**75** **<u>የይግባኝ አቤቱታን ለሌሎች ማሳወቅ</u>**

ኮሚሽኑ የይግባኝ አቤቱታው እንደደረሰው ጉዳዩ የሚመለከተውን ዳታ ተቆጣጣሪና ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎችን ስለ ቀረበው ይግባኝ ማሳወቅ አለበት።

**76** **<u>ሽምጋይ</u>**

ኮሚሽኑ የይግባኙን አቤቱታ እንዲመረምርና ጉዳዩን በስምምነት እንዲቋጭ ሽምጋይ ሊመድብ ይችላል።

**77** **<u>በኮሚሽኑ ስለሚደረግ ምርመራ</u>**

(1) ኮሚሽኑ የዳታ ተቆጣጣሪውን ውሳኔ በተመለከተ

(ሀ) ሽምጋዩን ምርመራ እንዲያካሂድ ያልፈቀደለት ከሆነ፣ ወይም

(ለ) ሽምጋዩ ምርመራ እንዲያካሂድ ፈቅዶ ከሆነና፣ ነገር ግን ምንም ዓይነት ስምምነት ላይ ያልተደረሰ ከሆነ ምርመራ በራሱ ሊያካሂድ ይችላል።

(2) ኮሚሽኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ምርመራ በሚያካሂድበት ጊዜ በምርመራው ማጠቃለያ ላይ

(ሀ) የዳታ ተቆጣጣሪው ውሳኔን ያጸናል፣

(ለ) የዳታ ተቆጣጣሪው ለአቤቱታ አቅራቢው እንደ አቤቱታው እንዲፈጽም ማዘዝ ይችላል፤ ወይም

(ሐ) ሌላ አግባብ ያለው ውሳኔ በመወሰን በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም ማዘዝ ይችላል።

**78** **<u>በግል የሚካሄዱ ስብሰባዎች</u>**

ኮሚሽኑ ወይም ሽምጋዩ የሚያደረጓቸው ማንኛውም ስብሰባዎች በዝግ ሊካሄዱ ይችላሉ።

**79** **<u>በምርመራ ጊዜ የሚደረግ ውክልና</u>**

https://chilot.me



በዳታ ተቆጣጣሪው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ያቀረበ፣ ወይም የኮሚሽኑን፣ የዳታ ተቆጣጣሪው ኃላፊዎችን፣ ወይም የሌሎችን አካላት ትብብር የሚጠይቅ የዳታ ባለቤት በጠበቃ ወይም በሌላ ወኪል ሊወከል ይችላል።

**80 <u>የማስረዳት ግዴታ</u>**

የዳታ ተቆጣጣሪው የዳታ ባለቤቱን ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ኢንፎርሜሽኑ በአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ላይ በተጣሉ ገደቦች በአንዱ ውስጥ የሚወድቅ መሆኑን የማረጋገጥ ሸክም የሚያርፈው በዳታ ተቆጣጣሪው ላይ ነው።

**81 <u>ለፍርድ ቤቶች የሚቀርብ ይግባኝ</u>**

የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በኮሚሽኑን ውሳኔ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።

## ምዕራፍ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**82. <u>የአሠራር ደንቦች</u>**

(1) ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን የግል ዳታን የማቀናበር መርሆዎችን ተግባራዊነትን ለማጎልበት ከሚመለከተው ዘርፍ ጋር መወያየት አለበት ።

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት፣ ኮሚሽኑ ከሌሎች ተግባርና ኃላፊነት ባሻገር

- (ሀ) የአሠራር ደንቦችን እንዲቀረጽ መመሪያ ይሰጣል፣
- (ለ) አቤቱታዎች ምላሽ የሚሰጥባቸውን አግባቦችን በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል፣
- (ሐ) በግል ዳታ ጥበቃ መርሆዎች ዙሪያ የሚሰጡ ትምህርቶችን ያበረታታል፣
- (መ) በሸማቾች መካከል የአሠራር ደንቦችን በተመለከተ ግንዛቤ ለማሳደግ ከመንግስት እና ከግል አካላት ጋር ይሠራል፣ እንደዚሁም
- (ሠ) ኮሚሽኑ ተገቢ መስሎ የታየውን ማንኛውንም ሌሎች እርምጃ ይወስዳል።

(3) ኮሚሽኑ በአንድ ዘርፍ ወይም ሙያ ውስጥ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አስገዳጅ የሆነ የአሠራር ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ፣ የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ የአሠራር ደንብ እንዲዘጋጅ ኮሚሽኑ በመመሪያ ሊደነግግ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔውን ሊያሳውቅ ይችላል።

(4) በንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተውን ለመፈጸም ዘርፉን ወይም ሙያውን የሚመራ የመንግሥት ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ካለ፣ ለዘርፉ ወይም ለሙያው የአሠራር ደንብ እንዲያወጣ ኮሚሽኑ ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል።

**84. <u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

**85. <u>የሽግግር ደንቦች</u>**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተገኙ የግል ዳታዎች እንደዚሁም ጥንቃቄ የሚፈልጉ የግል ዳታዎች የሚቀናበሩት ወይም በቀጣይ የሚቀናበሩት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አግባብ ብቻ ነው።

**86. <u>የዳታ ተቆጣጣሪዎችና የዳታ አቀናባሪዎች ግዴታዎች</u>**

በዚህ አዋጅ በዳታ ተቆጣጣሪዎች ላይ የተጣለ ግዴታ እንዳግባብነቱ በዳታ አቀናባሪዎች ላይም ተፈጻሚ ነው፡፡

**87. <u>የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኮሚሽኑን ውሳኔዎች በይግባኝ እንዲመረምር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**88. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ኮሚሽኑ ከዚህ አዋጅ በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**89. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው የአዋጁ ዓላማ እንዲሳካና ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መፈጸም እንዲችል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**90. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ __________ ቀን 2012 ዓ/ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት